# ፀረ ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ፀረ ሙስና | ቅጽ 1 ቁጥር 4 ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም


## ኮሚሽኑ የፌደራል የመንግስት ባለስልጣናት የሥነ-ምግባር ረቂቅ ደንብ እና የጥቅም ግጭትን ለመከላከል፣ለማስወገድ እና ለማስተዳደር በወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሄደ



ሀገሪቱ የጀመረችው የፀረ-ሙስና ትግል ፍሬያማ እንዲሆን የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ቁርጠኝነት እና ተሳትፎ ሊጎለብት እንደሚገባ የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

ኮሚሽኑ የፌደራል የመንግስት ባለስልጣናት የሥነ-ምግባር ረቂቅ ደንብ እና የባለስልጣናት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል፣ ለማስወገድ እና ለማስተዳደር በወጣ ረቂቅ ደንብ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተወያይቷል፤ ረቂቅ ደንቦቹ ባለስልጣናቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እና ስነምግባርን በተላበሰ መልኩ እንዲወጡ የሚያስችሉ መሆናቸው በውይይቱ ላይ የተገለፀ ሲሆን፣ የሥራ ኃላፊዎች የሀገር እና የህዝብን ሀብት ከሙስና በፀዳ መልኩ እንደሚጠቀሙ እና ተጠያቂነትን ለማስፈን መዘጋጀታቸው ገልፀዋል፡፡

የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶክተር ሳሙኤል ኡርቃቶ ሙስና በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህንም ለመቅረፍ መንግስት እንደ ሀገር ትኩረት አድርጎ እየሰራ ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል መሆኑን




አብራርተው፣ የፀረ-ሙስና ትግሉ ፍሬያማ እንዲሆን የመንግስት የስራ ኃላፊዎች የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡ በፀረ ሙስና ትግሉ የስራ ኃላፊዎችን ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ የባለስልጣናት የሥነምግባር ረቂቅ ደንብ እና የባለስልጣናት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያግዙ ረቂቅ ደንቦች መዘጋጀታቸው አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የኮሚሽኑ የሕግ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ረቂቅ ደንቦች በሀገሪቱ የሚስተዋሉና ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ለመፍታት ያግዛሉ ብለዋል፡፡ በረቂቅ ደንቡ ሁለት አዳዲስ ድንጋጌዎች መካተታቸውን በመጥቀስ ባለስልጣናት ከኃላፊነት ከለቀቁ በኋላ ሊኖራቸው ስለሚገባ ስነምግባር እና ሚስጥር ጠባቂነት የሚዘረዝር ድንጋጌ መኖሩን አመላክተዋል፡፡ ሌላኛው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የተሰጣቸውን ሀገራዊ ግዴታ ከፖለቲካ እንቅስቃሴያቸው ጋር አስታርቀው መሄድ የሚችሉበትን መንገድ የሚደነግግ ስለመሆኑም ጠቁመዋል፡፡

የኮሚሽኑ ም/ኮምሽነር አቶ ወዶ አጦ እንዳሉት የመንግስት ባለስልጣናት በሚፈለገው መልኩ ለደንቡ

ኮሚሽኑ የፌደራል ... ወደ ገጽ 2 የዞረ

## ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም ከባድ የሙስና እና አስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈፅመዋል በተባሉ 3 የፖሊስ አባላት ላይ ክስ ተመሰረተ

ዐቃቤ ሕግ በአዲስ አበባ ፖሊስ የአየር መንገድ ፖሊስ ጣቢያ የወንጀል ምርመራ ኃላፊን ጨምሮ ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀም ከባድ የሙስና እና አስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽመዋል ባላቸው 3 የፖሊስ አባላት እና ግብረ-አበሮቻቸው ላይ ክስ መሰረተ፡፡

ዐቃቤ ሕግ ክስ የመሰረተውም 1ኛ ተከሳሽ ም/ኢንስፔክተር መንግስቱ ገብረሚካኤል አልባሞ 4ኛ ተከሳሽም ጉዳዩን በሕጋዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ከ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር በመመሳጠር 3ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ሰራዊት አባልነቱን በመጠቀም የወታደራዊ ደንብ ልብስ እንደለበሰ ካልተያዙት ግብረ አበሮቹ ጋር ወደ መኖሪያ ቤቷ በመሄድ በተበዳይዋ ላይ ዛቻ እና ማስፈራራት ፈጽመዋል፡፡ ከዚህ ባለፈም በማሳሰር ብሎም ከታሰረችበት የፖሊስ ጣቢያ ሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 10፡30 ሰዓት ሲሆን ወደ አየር መንገድ ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ "ንብረቱን ካልመለሽ ክሱን ወደ ሽብር ወንጀል እንቀይረዋለን፣ እናሳይሻለን" በማለት ያስፈራሯታል፡፡

ቀጥሎም ከተበዳይ የግል ስልክ ላይ ንብረቱ ይገኝበታል ያሏቸውን ስልክ ቁጥሮች ከወሰዱ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የአየር መንገድ ፖሊስ ጣቢያ የሴት እስረኛ ማቆያ እንደሌለው እያወቁ ሆን ብለው ለሌላ አገልግሎት ከሚጠቀሙበት መብራት እና መኝታ ከሌለው፣ በሩ ከውስጥ ከማይዘጋ እና ደህንነቱ

ስልጣናቸውን ያለአግባብ ... ወደ ገጽ 2 የዞረ

## ኮሚሽኑ በፍርድ ቤት ዘርፍ በተካሄደ የሙስና ስጋት የዳሰሳ ጥናት ላይ ስልጠናዊ ውይይት አካሄደ

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ኮሚሽኑ ሙስና እንደ ሀገር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ የእድገትና የመልካም አስተዳደር ማነቆ ሁኖ ይስተዋላል፣ መንግስትም ችግሩን ለመቅረፍ በየግዜው የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት እየሰራ ይገኛል ያሉ ሲሆን፣በ2014 ዓ.ም በፍርድ ቤቶች በአመራርና በሙያተኞች የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የአሰራር ስርዓት ጥናት ያካሄደ መሆኑን አስታውሰው፣ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነፃነታቸውን ጠብቀው የሀገራችንን ህዝቦች ሰላምና ፍትህ ለማረጋገጥ፣ የዜጎችን እንግልት ለመቀነስ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የፍርድ ቤቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን በውይይቱ ለተገኙት የፍርድ ቤት የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡

ኮሚሽኑ በፍርድ ቤት... ወደ ገጽ 2 የዞረ





## ስልጣናቸውን ያለአግባብ ...

ባልተጠበቀ ባዶ ክፍል ውስጥ እንድታድር ያደርጋሉ። በዚያው ዕለት የአዳር ተረኛ ጥበቃ በመሆን ተመድቦ ሲሰራ የነበረው 5ኛ ተከሳሽ ከምሽቱ 5 ሰዓት አካባቢ የፖሊስ መለዮውን እንደለበሰና የጦር መሳሪያ እንደያዘ የግል ተበዳይ ያለችበትን ክፍል በር ከፍቶ በመግባት ‹‹ብትጮሂም ምንም አታመጪም፣ ማንም አይደርስልሽም፣ የግቢውን በር ቆልፌዋለሁ፣ ብቻዬን ነኝ፣ እጮሃለሁ ካልሽ በዚህ ክላሽ እመታሻለሁ›› በማለት የግል ተበዳይን በብርቱ ዛቻ በማስፈራራት መከላከል እንዳትችል በማድረግ አስገድዶ ደፍሯታል። ከደፈራት በኃላም በሩን ዘግቶ በመውጣት ከአንድ ሰዓት በኋላ ተመልሶ በመምጣት ተመሳሳይ ድርጊት የፈፀመባት ሲሆን፤ የግል ተበዳይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከተፈጸመባት በኋላም እዛው ክፍል ውስጥ ለ3 ቀን እንድታድር 1ኛ ተከሳሽ ትዕዛዝ በመስጠት፣ 2ኛ ተከሳሽ ደግሞ ንብረቱን ብትመልስ እንደሚሻላት በመዛት፣ ንብረቱን አስቀምጦ የነበረው ግለሰብ በወንጀል ባልተጠረጠረበትና ክስ ባልቀረበበት ሁኔታ በማታለል በወንጀል እንደተጠረጠረ አስመስለው በ1ኛ ተከሳሽ ትዕዛዝ ሰጪነት የብርበራ ትእዛዝ አውጥተው በመኖሪያ ቤቱ ብርበራ አድርገዋል።

በመቀጠልም ለጊዜው ያልተያዙ ተጠርጣሪዎች የግለሰቡ መኖሪያ ቤት ላይ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-56045 ኦ.ሮ የሆነ ዶልፊን መኪና እስከ ለሊቱ 6 ሰዓት በማቆም ጫና በመፍጠር፣ ከፍተኛ ዛቻ እና ማስፈራሪያ በመፈጸም 4ኛ ተከሳሽ ንብረቱን የተቀበለ በመሆኑ፣ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4 ኛ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈፀሙት በስልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል 5ኛ ተከሳሽ ደግሞ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶባቸዋል።

በተጨማሪም 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሽ ንብረቱ እሱ ጋር ይሆናል ብለው ያሰቡትን አቶ ቢኒያም ጳውሎስን ንብረቱን እንዲሰጣቸው በተደጋጋሚ ሲዝቱና ሲያስፈራሩት ቆይተው በሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ሰዓቱ በውል ባልታወቀ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወንድማማቾች ስጋ ቤት አካባቢ 3ኛ ተከሳሽ ለጊዜው ካልታወቁ የመከላከያና የአዲስ አበባ ፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ 5 ሰዎችና ሌሎች 2 ግለሰቦች ጋር በመሆን የግል ተበዳይ አቶ ቢኒያም ጳውሎስን ለመያዝ በመኪና በማባረር አራት ጥይቶችን በመተኮስ ከያዙት በኋላ 3ኛ ተከሳሽና ለጊዜው ያልተያዙት ተጠርጣሪዎች በመሳሪያ እየደበደቡ መኪና ውስጥ አስገብተው አይኑን በጨርቅ አስረው ወደ ጎልፍ ክለብ ወስደውታል።

በዚህም ከሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ በሕገ ወጥ መንገድ ጨለማ ክፍል ውስጥ ለ15 ቀናት አስረው ካቆዩት በኋላ ንብረቱን በኃይል ስላስመለሱ የግል ተበዳይን የለቀቁት በመሆኑ ሁለቱም ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈፀሙት በስልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ህግ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ጥቅምት 8 ቀን 2015 ቀን ክስ መስርቶባቸዋል። የክሱ ማመልከቻ ደርሷቸው ከጠበቃ ጋር ለመቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ በጠየቁት መሰረት ፍርድ ቤቱ ተለዋጭ ቀጠሮ የሰጣቸው መሆኑንም ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# ኮሚሽኑ በፍርድ ቤት ዘርፍ በተካሄደ ...

አቶ ወዶ አጦ አክለውም ፍርድ ቤቶች አስፈፃሚውንም ሆነ ህግ አውጪውን ቁመና በህግ መግዛት የሚችሉ ተቋማት በመሆናቸው፣ ህዝቡ የሚተማመንባቸው ግልፅነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ ተቋማትን ለመገንባት ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ፣ የሚከላከልና የሚያጋልጥ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን፣ ሆኖም የተጣለባችሁን ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊነት በተጠያቂነት ስሜት መወጣት ይገባል ብለዋል፤ ኮሚሽኑ አቅም በፈቀደው ሁሉ አቅሙን በማሟጠጥ የተሻለ ስራ ለመስራት አገራዊ የሙስና ትግሉን በማቀጣጠል ወደ ስራ የምንገባበት ወቅት አሁን እንደሆነ ለተወያይዎች መልክት አስተላልፈዋል።



የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ክብርት ወ/ሮ ዘላለም ለማ በአስተላለፉት መልዕክት በሀገራችን ብሎም በክልላችን በተለያዩ ዘርፎች የታዩ ድሎችን ቀጣይነት ለማረጋገጥና የሚጠበቅብንን ለመወጣት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመታገል በተግባር ማስቀጠል ይኖርብናል ያሉ ሲሆን፣ ይሁንና ለሰላም፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሚደረገው ጥረት በሙስና እንዳይደናቀፍ በታላቅ ህዝባዊ ተሳትፎ የፀና የመንግስት ተቋም ለመገንባት ጠንካራ የፍርድ ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ያስፈልጋሉ፣ ሆኖም ህዝቡ ከመንግስት ብሎም ከዳኝነት አካሉ የሚፈልገውን ፍትህ ከሙስና በፀዳ መልኩ እንዲያገኝ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከልና የማጋለጥ ተግባር የፍርድ ቤቶች የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በኃላፊነትና በታማኝነት መወጣት ይገባል በማለት አብራርተዋል።

የፌዴራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደ ሀገር በተመረጡ ተቋማት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ የሙስና ስጋት ደረጃዎችን እንዲጠኑ በማድረግ ተግባር ተኮር የስነ ምግባርና የሙስና መከላከል ስልጠናዎችን በመስጠት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ኮሚሽኑ በፍርድ ቤቶች በሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች ባስጠናው ዳሰሳዊ ጥናት ከ400 በላይ የሚሆኑ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች ስልጠናዊ ውይይት ያካሄደ ሲሆን፣ በጥናቱ የሙስና ወንጀል በኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ እያደረሰ መሆኑን የተጠቆመ ሲሆን፣ ጥናቱ በተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች ያለአግባብ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለትና ጥፋተኛውን ደግሞ ነፃ መልቀቅ፣ የዋስትና መብት መከልከልና መስጠት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚስተዋሉ ተነስቷል።

በጥናቱ በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ፣ በፍርድ አፈፃፀምና በሬጂስትራር አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተለዩ የሙስና ስጋቶች፣ መንስኤዎችና የመፍትሄ ሃሳቦች ተዳሰዋል። የሙስና ስጋት ጥናት ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው በፍ/ቤቶች አሰራር የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችን ለመቅረፍ የበላይ አመራሩ ከሁሉም የባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቁርጠኝነት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ይጠቁማል።

በውይይት የቀረበው የፍርድ ቤት የሙስና ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ላይ የተገኙ ግኝቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የዘርፉን የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ስራ አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች ለስልጠና፣ ለሙስና መከላከል፣ ጥናት ለማድረግና ለሙስና መረጃ ማመንጨት ፋይዳው የጎላ መሆኑን ተሳታፊዎች ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የስትራቴጂክ ፖሊሲ ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ስልጠናዎችን ይሰጣል። ፍርድ ቤቶች በግልፅነት፣ በታማኝነትና በተጠያቂነት ከሙስና የፀዳ የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን የፌዴራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በዉይይቱ ለተገኙ ተሳታፊዎች በማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ ገልፀዋል።

ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ አክለውም በፍርድ ቤት ዘርፍ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት የተለዩ የስራ ክፍሎችን ሀብት የማጣራት ስራ ይሰራ፣ ለፍትህ ፈላጊው የህብረተሰብ ክፍልም ፍትህ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባል፤ ከዚህ ባለፈ በልዩ ሁኔታ የሚታይ ዘርፍ በመሆኑ መንግስት ሪፎርሙ ጠንከር ያለ እንዲሆን አቅጣጫ ማስቀመጡን አብራረተዋል። ስለዚህ የዳኝነት አገልግሎቱ ከሙስና ስጋቶች የፀዳ ለማድረግ በትጋት መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ነፃና ገለልተኛ ሆነው የዳኝነት አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ የፀረ-ሙስና ትግላቸው የሙሰኞችን ሰንሰለት መበጣጠስ እንዲችል የሚያሰራ ወጥነት ያለው አደረጃጀት በመፍጠር በአቅም ግንባታ ስልጠናና በአመለካከት በልጠው መገኘት ይኖርባቸዋል ብለዋል። ለዚህም ኮሚሽኑ ችግር ፈቺ የሆነ የፍርድ ቤት የሥነ-ምግባር አስፈፃሚዎች አቅም የሚያጎለብትና የህብረተሰቡን ንቃተ ህሊና የሚያሳድግ ስልጠና ያዘጋጃል፣ ሆኖም በእናንተ በኩል 95 በመቶ በመከላከል ላይ ያተኮረ ስትራቴጂያዊ ስራን የመስራት፣ የመጠቆም፣ የማጋለጥና ሀብት የማስመለስ ስራን በጋራ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት ባህላችንን አዳብረን ከሙስና በፀዳና መልካም ሥነምግባርን በተላበሰ መልኩ ከአመራሮቻችሁ ጋር በመግባባትና በመተባበር መስራት እንደሚገባ ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አመላክተዋል።

በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የሲዳማ ብ/ክ/መንግስት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ክቡር አቶ በየነ በራሳ መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፣ የሀገራችንን የልማት፣ የዲሞክራሲ፣ የሰላምና የፍትህ ጉዞ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ገልፀው፣ ይሄን ጉዟችንን ለማስቀጠል እንቅፋት የሆነብንና ትግላችንን የሚያቀጭጭ ሙስናን መከላከል ይገባል፤ ስለሆነም በፍርድ ቤት ዘርፍ የምትገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ለዕድገታችን ፀር የሆነውን ሙስና ለመከላከል፣ ለመጠቆም፣ለማጋለጥ፣የዳኝነት አገልግሎቱ የህዝብ አመኔታንና እርካታን ለመፍጠር እንዲሁም ፍትህ እንዲሰፍን ያላችሁ ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተገንዝባችሁ ትግሉን እንድታፋጥኑ ለዚህም መንግስት ከጎናችሁ መሆኑን እገልፃለሁ ብለዋል።

## ኮሚሽኑ የፌደራል የመንግስት ባለስልጣናት ...

ተገዥ በማድረግ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ማስፈን ያስፈልጋል፣ ኮሚሽኑ ከሚሰራቸው ስራዎች አንዱ የመንግስት ስራ አስፈጻሚዎች በሚሰጡት አገልግሎት ተጠያቂነትን ማረጋገጥ እና የመረጃ ነጻነትን በሚመለከት እንደመሆኑ የተዘጋጀው ረቂቅ ደንብ ተፈጻሚ ከተደረገ በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚያገኙም አብራርተዋል።

በውይይቱ የተሳተፉ የተቋማት ተወካዮች ረቂቅ ደንቦቹ ኃላፊነት ላይ የተቀመጡ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ህዝብ እና መንግስት የጣሉባቸውን አደራ በአግባቡ እንዲወጡ ያስችሏቸዋል ነው ያሉት። የወጡት ሁለት ረቂቅ ደንቦች ፀድቀው ወደ ተግባር እንዲገቡ በመጠየቅ ለዚህ ደግሞ የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ቁርጠኝነትን ይጠይቃል ነው ያሉት።

ረቂቅ ደንቦቹ ተቋማቸው በየጊዜው ለሚያደርገው የቁጥጥር ስራ አጋዥ መሆናቸውንና ሁሉም ሰው ከህግ በታች በመሆኑ ደንቡ አስፈላጊ መሆኑን ያነሱት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ ናቸው። ከረቂቅ ደንቡ ባሻገር ሙስናን ለማጥፋት መንግስት የዲሞክራሲ ተቋማትን በማጠናከር ተጠያቂነት ማስፈን ያስፈልጋል በማለት አብራርተዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ህዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም ዋና እምባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ሀይሌ አዲስ የተዘጋጀውን ደንብ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ፣ መንግስት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ምቹ ከማድረግ አንፃር የራሱን አስተዋፆ ማበርከት ይችላል ብለዋል። በረቂቅ ደንቡ ላይ የተቀመጡት የስነምግባር መርሆች በህገ-መንግስቱ ዉስጥ፣ በተለያዩ መመሪያዎች እና አዋጆች ላይ ሰፍረው የሚገኙ ናቸው ብለዋል።

ባለስልጣናቱ የስነምግባር ጥሰት የሚፈጽሙት ህጉ ስለሌለ ወይም ካለማወቅ አይደለም ያሉት ዶክተር እንዳለ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እስካልቻሉ ድረስ ደንብ ስለወጣ ብቻ የሚለወጥ ነገር አይኖርም ነው ያሉት።

በደንቡ ላይ በአብዛኛው የተካተቱት የመልካም አስተዳደር እሴቶች ናቸው ያሉት ዶክተር እንዳለ ትኩረት አድርጎ መሰራት የሚያስፈልገዉም አመለካከትን የመቀየር ስራ ነው ሲሉም አመላክተዋል። የወጣውን ደንብ ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ የማህበረሰቡን የመልካም አስተዳደር ችግር እና ጥያቄዎች መቅረፍ ያስችላል ሲሉም ጠቁመዋል።

የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ የመንግስት ባለስልጠናት በሚፈጠሩ መድረኮች ላይ ሌባ ሌባ ከማለት ባሻገር ራሱ ሌባ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ብለዋል፣ ሌባ የሆነ ሰው አመራር ሁኖ በመቀጠል የህዝብን ሀብት የሚዘርፍ፣ ብሎም ብልሹ አሰራሮችን የሚሰራ ከሆነ የሀገርን እድገት የሚጎዳ በመሆኑ ረቂቅ ደንቡ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል። የመንግስት ባለስልጣን የህዝብን ሀብት ሰርቆ ውጭ ድረስ በመሄድ ከሚታከም ቢሞት ይሻለዋል በማለት ለውይይቱ ተሳታፊዎች አብራርተዋል።

ሙስና በተጨባጭ የሚያሳየው በጣም አደገኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ሌቦች በግልፅ ህዝባችን አገልግሎት ለማግኘት ገንዘብ በመጠየቅ ላይ መሆኑን ያብራሩ ሲሆን የሃይማኖት ተቋማት፣ሲቪክ ማህበራት፣የፍትህ አካላት እና ሚዲያዎች እንዲሁም ህዝቡ ሙስናን መታገል እንዳለበት መልክት አስተላልፈዋል።

# የኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች "በደም የከበረ በላብ የታሰረ" በሚል መሪ ሀሳብ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሄዱ



የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና የኮሚሽን ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ ለውይይት የቀረበው ሰነድ ወቅታዊ ሀገራዊ ሁኔታን የሚያስቃኝ መሆኑን ገልፀው፣ ሀገራችን ያለችበትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ድልና ጉድለት በእኛነት ስሜት ድሏንም፣ ጉድለቷንም ወስደን ለሀገራችን መፃኢ የዕድገት ጉዞ በተሰማራንበት የሥራ ኃላፊነት በተጠያቂነትና በግልፅነት በጋራ በመስራት የበኩላችንን አስተዋፅኦ ማበርከት እንዳለበት አብራርተዋል።



የኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች የድሉም፣ የጉድለቱም ባለቤት እኛው ነን ስለዚህ በጋራ ለህሊናችን እንሰራለን በማለት "በደም የከበረ በላብ የታሰረ" በሚል ሀገራዊ ወቅታዊ ጉዳይ በቀረበ ሰነድ ላይ ጥቅምት 23/2015 ዓ.ም ባካሄዱት ውይይት ገልፀዋል። ሰነዱ ኮሚሽኑ የተሻለ ስራ እንዲሰራ ትኩረት ማድረጉ፣በግብርናው፣ በዲፕሎማሲው፣በሰላም፣በኢኮኖሚውና በማህበራዊው ዘርፍ መንግስት በቀጣይ ለመስራት በግልፅ በማስቀመጡ ሁላችንም በተሰማራንበት መስራት አለብን በማለት አብራርተዋል።

ሀገራችን ያሏትን ሀብት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ አውላ ካደጉት ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ የአብዛኛው ችግሯ መንስኤ የሆነውን ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል እንደሚያስፈልግ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ ጠቅሰው፣ ለሀገራዊ የዕድገት ፀር የሆነውን ሙስናን ለመከላከልም ኮሚሽኑ በህግ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት በአመለካከት የጋራ ግንዛቤ በመያዝ በቆራጥነት መስራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ሀገራችን ባለፉት አራት አመታት የገጠማትን ውስብስብ ችግሮች አልፋ አሁን ባለችበት ቁመና እንደምትገኝ ገልፀው፣ያሉንን ሀብቶች በተገቢው መንገድ በመጠቀም የብልፅግና ጉዟችን በማስቀጠል በድፕሎማሲው፣ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው እና በማህበራዊው ዘርፍ በጋራ ጠንክረን በመስራት ጠንካራ ሀገር መገንባት አለብን ብለዋል።

የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ ኢትዮጵያ የጋራ እንስራችን በመሆኗ በጋራ ማልማት አለብን፣ አድዋ የተዋደቀው ኢትዮጵያዊ ነው፣ ተከባብረን በመስራት ውስጣችን ማጠንከር ከቻልን ማንም የውጭ ኃይል ጣልቃ አይገባብንም በማለት ገልፀው፣ ኮሚሽኑ በተሰጠው ስልጣን ልክ አመራሩና ሰራተኛው በመቀናጀት ሙስናን መከላከል አለብን ያሉ ሲሆን፣ ከመድረኩ ለተነሱ ሀሳቦችና በጎ አስተያየቶች መንግስት እንደግብዓት ወስዶ እንዲጠቀምበት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

# በደቡብ ክልል በህገ-ወጥ መንገድ የደረጃ እድገትና ቅጥር ላይ በተካሄደ የማጣራት ስራ ከ120 ሚሊዮን ብር በላይ ከብክነት ማዳን መቻሉ ተጠቆመ

በደቡብ ክልል በጎፋና በወላይታ ዞን በተደረገ የመንግስት ሰራተኞችና አመራሮች በደረጃ እድገትና በቅጥር፣ በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እንዲሁም በሀሰተኛ የብቃት ማረጋገጫ (ሲኦሲ) በተደረገ የማጣራት ስራ ከ120 ሚሊዮን ብር በላይ ከብክነት ማዳን መቻሉን የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀይል ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መኮነን ደስታ ገልፀዋል።

የክልሉ መንግስት ለስራው ትኩረት በመስጠት ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ እንዲሁም ከሌሎች ተጠሪ ተቋማት ጋር ውይይት በማድረግ በተደረሰው ስምምነት መነሻ በማድረግ ካለፉት አመታት በተለዩ አመራሩ ቁርጠኛ በመሆን ስራውን ያከናውናሉ ተብለው ከተለያዩ የዞኑ መስሪያ ቤቶች 5 አባላትን ያካተተ ኮሚቴ አዋቅሮ ወደ ስራ የገባ መሆኑን አብራርተዋል።

በጎፋ ዞን በሚገኙ በ10 ወረዳዎች፣ በ4 ከተማ አስተዳደርና በ7 የገጠር ወረዳ መረጃወን የማጣራት ስራ የተገባ ሲሆን፣ ከተመረመሩት 26,236 ፋይሎች መካከል 4,249 መረጃዎች ብልሹ አሰራር መኖሩን ተመላክቷል። ከነዚህ መካከል 25 በመቶ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ያለቸው ሲሆን፣ 105 ሰራተኞች ህጋዊ ሳይሆኑ የመንግስት ደሞዝ በየወሩ ሲወስዱ የነበሩ ቅጥራቸው እንዲሰረዝ ተደርጓል ብለዋል።

ከተጣሩት ማስረጃዎች መካከል ያለ አግባብ የደረጃ እድገት የተሰጣቸው፣ ቅጥር የተፈፀመላቸው እና በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተቀጠሩ ሰራተኞች ሙሉ በሙሉ እንዲሰረዙ ተደርጎ ከ82 ሚሊዮን 905 ሺ ብር በላይ ማዳን መቻሉን ተብራርቷል።

ህገ-ወጥ የትምህርት ማስረጃዎችን ለሰራተኞች በመስጠት ችግር ፈጥረዋል የተባሉ 12 ተቋማት ማስቆም ሲቻል ለ5 ተቋማት ደግሞ ማስጠቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል።

የዞኑ የሰው ሀብት ልማት ኃላፊ አቶ መኮነን ደስታ እንደገለፁት ከግል ኮሌጆች ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተማሪዎች ውጤታቸው በጣም የሚያስፈራና 3.80 እና በላይ የሆኑ ሲሆን፣ ይህን ተማሪ ከተማርካቸው ትምርቶች ሁለቱን ጥቀስ ብተለው እንደማይገልፅ ያብራሩ ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ድግሪ በመግዛት መምህር በመሆን ተማሪዎችን የሚያስተምር ከሆነ ምን አይነት ትውልድ ነው የሚያፈራው ያሉ ሲሆን፣ አንድ የጤና ባለሙያ ህክምና አገልግሎት ሊሰጥ በጤና ዘርፍ ድግሪ የሚያመጣ ከሆነ ምን አይነት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል በማለት አብራርተዋል። የመንግስትን ገንዘብ ያለ አግባብ በአንድ መደብ ላይ ከአንድ ሰው በላይ ዘጠኝና አስር ሰው በመቅጠርና በካቢኔ በመወሰን በዚህ ልክ ደሞዝ እየከፈልክ የምትሄድ ከሆነ ህዝቡ ለሚያነሳው የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ በቂ ምክኒያት የሚሰጥበት ምቹ ግራውንድ በፍፁም የለህም በማለት አብራርተዋል።

በጎፋ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት የስነምግባር ባለሙያ የሆኑት አቶ ተስፋዬ እስጢፋኖስ የተቋማት አመራር የትምህርት ማስረጃ ችግር ካለበት እንዴት በስሩ ያሉ ሰራተኞችን መቆጣጠር ይችላል ያሉ ሲሆን፣ የማጣራት ስራዎችን ሲሰሩ የነበሩ ኮሚቴዎች ዛቻና ማስፈራሪያ ቢደርስባቸውም ጫናውን በመቋቋም ተግባሩን ማከናወን እንደቻሉ አብራርተዋል።

ከጎፋ ዞን በተጨማሪ በወላይታ ዞን የአመራርና የሰራተኞችን ፋይል ማጣራት መቻሉን የዞኑ የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ሃላፊ ወ/ሮ ፀጋ ፈንታ የገለፁ ሲሆን፣ ህገወጥ ዝውውር፣ የደረጃ እድገትና ቅጥር የተፈፀመላቸው እንዲሁም በህገወጥ የትምህርት ማስረጃ የተቀጠሩ ሰራተኞች ተቋሙ ሰነዳቸውን መርምሮ ውሳኔ ከመድረሱ በፊት ራሳቸውን ለመንግስት እንዲያጋልጡ በአካባቢው ባሉ የመገናኛ ዘዴዎች መልክት እንዲተላለፍ ተደርጎ ወደ ስራ እንደተገባ አብራርተዋል።

በዞኑ ከ90 ሺ የሚበልጡ ከተለያዩ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ተመርቀው በስራ አጥነት የሚገኙ ቢሆንም ሌሎች ያለአግባብ በመመሳጠር በአቋራጭ እየተቀጠሩ እንደሆነ ጠቁመው፣ በዞኑ እስካሁን በተካሄደው የማጣራት ስራ በርካታ የትምህርት ማስረጃዎችን መመርመር የተቻለ ሲሆን፣ በዚህም መነሻ የተለያዩ ግኝቶች መገኘታቸውን አመላክተዋል።

በዞኑ 2,485 ማህደር የማጣራት ስራ የተሰራ ሲሆን፣ 594 ሰራተኞች የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ ሁኖ እንደተገኘ፣ 102 ሰራተኞች ደግሞ የብቃት ማረጋገጫቸው ህገወጥ ሁኖ የተገኘበት ሂደት መኖሩን ጠቅሰው፣ ቋሚ ቅጥር መፈፀም እያለበት በኩትራት የተቀጠሩ 171 ሰራተኛ ሲኖሩ፣ መደብ በሌለበትም 57 የኩትራት ቅጥር የተቀጠረበት አግባብ እንዳለ ገልፀው፣ በዚህ ሂደት በተሰራ ስራ ከ37 ሚሊዮን 258 ሺ ብር በላይ ከብክነት ማዳን መቻሉን አብራርተው፣የሁሉም ሰራተኛ መረጃ ሲፈተሽ የሚወጣው ነገር ቀላል እንዳልሆነ ከዚህ በመነሳት መረዳት ይችላል ብለዋል።

በወላይታ ዞን ከ52,920 በላይ የመንግስተ ሰራተኞች ሲኖሩ ያጠቃላዩን ሰራተኛ መረጃ የማጣራት ስራ የሚከናወን ይሆናል ያሉ ሲሆን፣ ችግሮች የተገኙባቸው አመራርና ሰራተኞች ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስራ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በጋራ የሚሰራ እንደሚሆን የዞኑ የሰው ሀብት መምሪ ሃላፊ ወ/ሮ ፀጋ ፈንታ አብራርተዋል።

በክልሉ ባሉት ተቋማት በዚህ ሂደት የተሳተፉ አካላትን በህግ እንዲጠየቁ ከማድረግ አንፃር 42 አመራር አካላት ከኃላፊነት ቦታቸው ሲነሱ 13 የአመራር አካላት ከደረጃቸው ዝቅ እንዲሉ ተደርጓል ያሉ ሲሆን፣ ከአንድ እስከ ሶስት ወር ደሞዝ የተቀጡ ባለሙያዎች እንዳሉ የደቡብ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀይል ልማት ቢሮ ምክትል ሃላፊ አቶ መኮነን ደስታ ገልፀው፣ በአጠቃላይ 1,054 አመራሮችና ባለሙያዎች በህግና አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን፣ በሌሎች አካባቢ ያሉ የመንግስት ተቋማት ይህን እያዩ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ የመጣበት አግባብ እንደአለ አብራርተዋል።

የደቡብ ክልል ፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀብት ልማት ምክትል ቢሮ ኃላፊው እንዳሉት በተለያዩ የመንግስት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አገልግሎቶቹን ፈጣን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ እንዲያስችል በክልሉ ባሉ በሁሉም የመንግስት ተቋማት እየተከናወኑ የሚገኙት የሰራተኞች የትምህርት ማስረጃን የመመርመር ስራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል በማለት አብራርተዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቶ ርስቱ ይርዳው በበኩላቸው በመንግስት ተቋማት በህግና በስርዓት የመመራት ክፍተቶችን ማረም እንደሚገባ አመልክተዋል። በተለይም በቅጥር ስርዓት ላይ እየተስተዋለ ያለው በህገወጥ የትምህርት ማስረጃ የሚፈፀም ቅጥር፣ሌብነት፣ ያለአግባብ የሚፈፀም የደረጃ እድገትና ምዘና ጨምሮ ሌሎች ህገወጥ ተግባራትን ማስወገድ እንደሚገባ አሳስበዋል። አሰራርን በማዘመን ተግባራትን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባም ርዕሰ መስተዳደሩ አስገንዝበዋል በማለት የክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ አስታውቋል።

# ኮሚሽኑ ሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመከላከል የሚያግዝ አገር አቀፍ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ተፈራረመ



የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመከላከል እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያግዝ አገር አቀፍ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በፌዴራል እንዲሁም በሁሉም ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መካከል የተፈራረመ ሲሆን፣ ስምምነቱ በዋናነት ተቋማቱ የጋራ የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራዎችን በተደራጀ አግባብ እንዲያከናውኑ የሚያግዝ ነው ተብሏል።

የፌደራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመከላከል እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያግዝ አገር አቀፍ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በፌዴራል እንዲሁም በሁሉም ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉ የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች መካከል የተፈራረመ ሲሆን፣ ስምምነቱ በዋናነት ተቋማቱ የጋራ የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራዎችን በተደራጀ አግባብ እንዲያከናውኑ የሚያግዝ ነው ተብሏል።

የፌዴራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ በዚሁ ጊዜ እንዳሉት፣ የሙስና ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በረቀቀ መልኩ እየተፈጸሙ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል። በመሆኑም ከፌዴራል ጀምሮ በሁሉም ክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉ





ኮምሽኖች ወጥ የሆነ አሠራርን በመዘርጋት ሕዝቡን እና መገናኛ ብዙኃንን ባሳተፈ መልኩ ሙስናን መከላከል እና ተጠያቂነትን ማስፈን ይጠበቅባቸዋል ተብሏል።

ስምምነቱ የፀረ-ሙስና ትግሉ ሀብትን በዲጂታል መንገድ በማስመዝገብ በጋራ ከክልሎች ጋር መሰራቱ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን እና አመርቂ ውጤት እንዲያስገኝ ያደርገዋል ያሉ ሲሆን፣በተለይም ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እንደሚሠራ ጠቅሰው፣ ከዚህ አኳያ ኅብረተሰቡ የሚጠበቅበትን ትብብር እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

በተጨማሪም በዘርፉ ከሚሠሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና ከሃይማኖት ተቋማት ጋር በመሆን የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማስፋት የትብብር ማዕቀፉ በእጅጉ እንደሚያግዝ አብራርተዋል።

ሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና ተፅዕኖዎች ላይ የሚያተኩሩ ጥናቶችን በሁሉም ዘርፎች በማካሄድ ዋና ዋና ጉድለቶችን ለመለየት እንደሚያግዝም ጠቁመዋል።

የስነምግባርና ፀረ ሙስና የክልል እና የከተማ አስተዳደር ኮሚሽነሮች በበኩላቸው፣ ስምምነቱ የሙስና እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በዘላቂነት ለመከላከል ሚናው የጎላ መሆኑን ገልፀው፣ በተለይም ወጥ የሆነ የአሠራር መመሪያ በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር ያግዛል ነው ያሉት።

# ኮሚሽኑ በአለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰሩ የአገሪቱ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲከናወኑ ከገንዝብ ሚንስቴር ጋር በመሆን አቅጣጫ አስቀመጠ



የፌዴራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ጠቅላላ በጀት ከ4 ቢለዮን ዶላር በላይ የሚገመት በአለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ በሀገሪቱ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ መከናወኑን በየጊዜው በመከታተል የፕሮጀክት ማረጋገጫ/ ቬሪፊኬሽን/ሪፖርት እንዲያቀረብ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ከሰባት የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ተቋማት ጋር ውይይት በማድረግ የስራ አቅጣጫን በጋራ አስቀምጧል።

የመንግስት ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑ ኮሚሽኑ በቁርጠኝነት እንደሚሰራ ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አሳስበው፣ እያንዳንዱ ፕሮጅክት በተያዘለት ጊዜና ሀብቱ በአግባቡ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በአረጋገጠና ወጭ ቆጣቢ ሆኖ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ እንዲከናዎን የሁሉም ፕሮጅክቶች ባለድርሻ አካላት የተጣለባቸውን ኃላፊነት በተቆርቋሪነት ስሜት ስራቸውን መወጣት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ አክለውም ያለንን ውስን ሀብት በአግባቡ ልንጠቀም ይገባል፣ እንደነዚህ አይነት በእርዳታ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ደግሞ ተጠናቀው በአግባቡ ለተገቢው አላማ እንዲውሉና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲደርሱ ኮሚሽኑ ተገቢውን የመከታተልና የማጣራት ስራ በመስራት ትክክለኛና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለአለም ባንክ እንደሚልክ ጠቁመዋል።

በውይይቱ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሪፖርት ቀርቦ ውይይት የተደረገ ሲሆን በአፈፃፀሙ የታዩ ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠል የተስተዋሉ ደካማ ጎኖችን ደግሞ እንዲስተካከሉ የጋራ አቅጣጫን በመያዝ ተጠናቋል።

ኮሚሽኑ በአለም ባንክ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲሰሩ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና ሌሎች ስራዎችን ለመስራት ከአለም ባንክ ጋር ስምምነት ወይም ፕሮቶኮል መፈራረሙ ይታወቃል።

# ኮሚሽኑ በትምህርት ዘርፍ በሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መፍትሄዎቻቸው ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አካሄደ







የፌደራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በትምህርት ዘርፍ በሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶችና መፍትሄዎቻቸው ላይ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከትምህርት ሴክተር የስራ ኃላፊዎችና ተወካዮቻቸው፣ ከመንግስት ዩንቨርሲቲዎች ፎረም ሰብሳቢዎች፣ ከኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን፣ ከመምህራን ማህበር ፕሬዝዳንት፣ ከሚዲያ አካላት፣ ከኢትዮጵያ ሐይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ ከፍትህ አካላት፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ከሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጥቅምት 24/2015 ዓ.ም በኢንተር ሌግዥሪ ሆቴል ምክክር አካሂዷል።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ ለተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ፣ የትምህርት ዘርፍ በአመለካከት የተሻለ ዜጋን ለመፍጠር ከሌሎች ዘርፎች የተለየ በመሆኑ ልዩ ትኩረት በመስጠት ትውልዱን በሥነምግባር ማነፅ እንደሚገባና የትምህርት ሴክተሩ እንደ ሀገር በትውልድ ላይ የሚሰራ በመሆኑ ትግሉ መቀጣጠል እንዳለበት ጠቁመዋል።

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የህግ፣ የፍትህና የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ በመክፈቻ ንግግራቸው ሲገልፁ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የምንችለው በጋራ መስራት ሲቻል እንደሆነ፣ የሪፎርም ስራዎች ሲሰሩም ከሙስና የፀዱ አሰራሮችን ተግባሪ የሆኑ ተቋማት የሚለዩበት መሆን እንዳለበት ጠቁመው፣ ለዚህም በመድረኩ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ወስደን መስራት እንደሚገባ፣ ጠንካራ ሀገር የሚኖረን ተቋማት ሙስናን በመከላከል ረገድ ጠንካራ መሆን ሲችሉ እንደሆነና ሀገራችንን ከፍ ለማድረግ በጋራ ሙስናን መዋጋት በ2015 ዓ.ም የመንግስት አቅጣጫ በመሆኑ ሁሉም የህዝብ ተወካዮች ቋሚ ኮሚቴ በተለይ የኦዲት ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ ትኩረት በመስጠት የሙስና ችግርን ለመቀነስ አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚገባቸው አመላክተዋል።

ኮሚሽኑ በትምህርት ዘርፍ በሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችና የመከላከል መንገዶች በሚል ያስጠናው የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት ያቀረቡት ዶ/ር ሞላ አለማየሁ ህግና ስረዓትን ያልተከተሉ የቅጥር ሁኔታዎችና የደረጃ እድገት ተጠቃሽ ቢሆኑም ከባድ የሙስና ወንጀሎች የሚፈፀምባቸው ዘርፎች መኖሩን አብራርተው፣ በጥናቱ 20 የሚሆኑ የሙስና ችግሮች የተለዩ ሲሆን በጣም ከባድ ተብለው የተፈረጁት የመምህራን በተደጋጋሚ ክፍል አለመግባት፣የሀሰት የትምህርት ማስረጃ መበራከትና የሙያ ፍቃድ አሰጣጥ እድሳትና ስረዛ መሆኑን ለተወያዮች አብራርተዋል። ሙስና በአሁኑ ጊዜ ከወንጀል አልፎ የገቢ ማግኛ ዘዴ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አስተያየት ሰጭወች ሙስና የትምህርት ስርዓቱን አሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሶታል ብለዋል፣ በትምህርት ሴክተር ያለው የሙስና ችግር ሀገር የሚያናጋና ትውልድ የሚገድል ነው ብለዋል። ትምህርት ብርሃናችን፣ ጉልበታችንና የእድገት መሰረታችን ሁኖ በሙስናና ብልሽ አሰራር ከተዘፈቀ በጣም አሳሳቢ መሆኑን አብራርተዋል። ተቋማት በኃላፊዎች ልክ ስለተሰፉ ለሚዲያ ክፍት አይደሉም ያሉ ሲሆን ወደ ጤና ተቋማት ለህክምና አገልግሎት ሲኬድ ከጥበቃው እስከ ኃላፊው ድረስ ሙስና ካልተሰጠ አገልግሎት የማየገኝበት ደረጃ ላይ ስለተደረሰ ሙስናን በጋራ ልንዋጋው ይገባል በማለት ተወያዮች አብራርተዋል።

ዶ/ር ነገሪ ሌንጮ እንዳሉት በትምህርት ዘርፉ በየደረጃው ያለው አመራር ቤታቸውን አውቀው ሊመሩትና ተጠያቂነት ሊያሰፍኑ እንደሚገባ ገልፀው፣ሙስና ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ማንም የሚታለፍና ከህግ በላይ መሆን እንደሌለበት አብራርተው፣ የዲሞክራሲ ተቋማትና ሚዲያዎች ለህዝብ ተወካዮች ተጠሪ በመሆናቸው ሙስናን ትክረት አድርግን በመስራት በቀጣይ አመት በተመሳሳይ ውይይት ስንገናኝ አሁን ካለንበት የሙስና ደረጃ መገኘት የለብንም በማለት መልክት አስተላልፈዋል።

የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አባሳደር ሽፈራው ሽጉጤ በበኩላቸው ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣የፈተና ስረቆት ችግር አለ እንላለን ነገር ግን ተጋላጭነታችን አናስወግድም፣ ለማስወገድ በህብረተሰብ ደረጃ በመነሳት እንጂ ሰዶ በማሳደድ ችግርን ማስወገድ እንደማይቻል ገልፀው፣ የህግ አካላት ችግር ፈጣሪውን በመያዝ ተጠያቂ ማድረግ እንዳለባቸው አብራርተዋል።

የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮምሽን ኮምሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርካቶ መንግስት በ2015 ዓ.ም ሙስናና ብልሹ አሰራር ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀዳሚ ችግር መሆኑን አምኖ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ሲሆን፣ የባለ ድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ተባብረን ሰርቄ እኖራለሁ የሚል ገለሰብን ተጠያቂ የሚሆንበትን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ልንሰራ ይገባል በማለት በውይይቱ ለተገኙት አካላት አብራርተዋል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች www.feaccdars.gov.et**

**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


# ርዕሰ -አንቀፅ

የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን መከላከልና መዋጋት ስራን ለመስራት ከፍተኛ ሀላፊነት የተሠጠው ተቋም ሲሆን እስካሁን ድረስ ባከናወነው ሠፊ ተግባር በሙስናና ብልሹ አሠራር የተነሳ በሀገሪቱ ሊከሰቱ የሚችሉ ከፍተኛ አደጋዎችን መከላከል፣ መቀነስና መታደግ ችሏል።

ይህን ተግባሩን በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የበለጠ አጠናክሮ ይቀጥላል፣ ለዚህም እንዲያመች የተለያዩ የሪፎርም ስራዎችን እያከናወነ ሲሆን፣ ከነዚህ የሪፎርም ስራዎች ውስጥ ተቋሙን ወደ ተሻለና ዘመናዊ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ስራ ማሸጋገር ሲሆን ለዚህም ተጨባጭ የዲጂታል ኢንፍራስትራክቸር የመዘርጋትና ምቹ የስራ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይገኛል።

የኮሚሽኑ ስራ ሀገራዊ ተልዕኮን ያዘለ በመሆኑ ከክልል የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር የተጀመረውን የጋራ ስራ አጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን፣ በየተቋማቱ የሚገኙ የሥነ ምግባር ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎችም በቴክኖሎጂ በማስተሳሰርና የተቋሙንም የውስጥ ሠራተኞችና አመራሮች የፈጣን መረጃ ልውውጥ ትስስር ስርዐት በመዘርጋት ስራዎች ፈጣንና ጊዜ ቆጣቢ ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረግ አመርቂ የሆኑ ጅምር ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል። እነዚህን ስራዎችን የበለጠ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፤ ለዚህ ስራ ስኬትም የተለያዩ አካላት ድጋፍና ቀና ትብብር እጅግ ወሳኝ እንደሆነ ኮሚሽኑ ያምናል።

በ2015 ዓ.ም ኮሚሽኑ እንደ ወሳኝ ቁልፍ ስራ አድርጎ በመወሰን ለመተግበርና ለመፈፀም በዕቅድ ከያዛቸው ስራዎች መካከል ስራው ከተጀመረ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረውና በተለያዩ አደናቃፊ ምክንያቶች እንዳይፀድቅና እንዳይተገበር ሲደረግ የነበረውን የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ጥብቅ የሥነምግባር ረቂቅ ደንብ እና የባለስልጣናት የጥቅም ግጭትን ለመከላከል፣ ለማስወገድ እና ለማስተዳደር ይረዳ ዘንድ የተዘጋጀውን ረቂቅ ደንብ የመጨረሻ ውሳኔ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ምላሽ አግኝቶና ፀድቆ ወደ ተግባር የሚውልበትንና ምናልባትም ሀገራችን በፈረመቻቸው ኮንቬንሽኖች፣ ድንጋጌዎች ውስጥ ወሳኝና አስገዳጅ ከሆኑትና ሀገራችን እስከዛሬ እንደ ከፍተኛ ድክመት ከምትነሳበትና ከምትገመገምበት እስካሁን ከወሰደቻቸው እጅግ ቆራጥ የፀረ ሙስና መዋጊያ እርምጃዎች ውስጥ ከፍተኛ እውቅና በዓለም ማህበረሰብ ዘንድ የሚያሰጣትንነው።

ኮሚሽኑ የተለያዩ ሀገራትን ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ ያዘጋጀውንና በቀጣይነት ለሌሎች ሀገራት ሞዴል ሊሆን የሚችል ሲሆን በተለያዩ መድረኮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሰፊ ውይይትና የማዳበሪያ ሀሳቦች ተሰጥተውበት የመጨረሻ ማጠቃለያ ላይ ደርሶ ሰነዱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በ2015 ዓ.ም በጀት አመት ስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስራ የሚከናወን ሲሆን፣ ለስራውም መጠናቀቅ የተለያዩ አካላት ቁርጠኛ አቋምና ውሳኔ ትብብር እንደሚያስፈልግ በኮሚሽኑ ይታመናል።

ኮሚሽኑ በ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት ከእስከዛሬ በተለየ ሁኔታ ሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን የመከላከልና የመዋጋት ስራውን አጠናክሮ ለመቀጠልና የጀመረውን አዳዲስ ሪፎርሞች እንዲቀጥል የሚያስችል የመንግስት ቁርጠኝነትን የሚያረጋግጥና « ጥርስ ያለው የፀረ ሙስና ኮሚሽን » እንደሚያቋቁም ሠሞኑን ይፋ ባደረገው ሠነድ «በደም የከበረች በላብ የታሠረች ሀገረ ኢትዮጵያን እንገነባለን» በሚል ርዕስ በተዘጋጀና ይፋ ሆኖ የኮሚሽኑ ሠራተኞችና አመራሮች ውይይት ተደርጎበት ከስምምነት በተደረሰበት ሠነድ ይፋ ያደረገ በመሆኑ፣ የስራው ባለቤት ኮሚሽኑ በመሆኑ፣ ይህን የመንግስት አዲስ አቅጣጫ የፀረ ሙስና ትግል ቆራጥ እርምጃ ወደተግባር የማዋል ኃላፊነት ስላለበት፣ ኮሚሽኑ ግባሩን የማስተባበርና የማስፈፀም ሀላፊነት ወስዶ የሚሰራ ይሆናል። ለዚህ የመንግስት አዲስ የፀረ-ሙስና ትግል አቅጣጫ ስኬት እውን እንዲሆን የተለያዩ ባለድረሻ አካላት ርብርብ ወሳኝ እንደሆነ ኮሚሽኑ አጥብቆ ያምናል።

ኮሚሽኑ በ2015 ዓ.ም እንደ አዲስ አቅጣጫ ከሚከተላቸው ሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን አጠንክሮ ለመከላከልና ለመዋጋት አዲስ ስልት የነደፈ ሲሆን፣ ይህም ተቋማትን የክልል መዋቅርን ታች ጀምሮ እስከ ፌደራል ያሉ ተቋማትን በ21 ዘርፍ ከፋፍሎ ለመስራት ወደ ተግባር ገብቷል።

ኮሚሽኑ በ2015 ዓ.ም በፍርድ ቤቶች፣በገቢዎችና ጉሙሩክ የሙስና ስጋት ጥናት በማስጠናት ከሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት ጋር በመወያየት የጋራ መግባባት መድረስ ችሏል። በተለዬ መልኩ የትምህርት ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሠራር ለአጠቃላይ ሀገሪቱ ህልውና እጅግ አደገኛ ከመሆኑ አንፃር ዛሬ ለተፈጠረው የትውልድ፣ የሞራልና የሥነምግባር ውድቀት፣ ክፍተት በትምህርት ዘርፍ ሆን ተብሎም ይሆን፣ በሌሎች የሀገሪቷ ታሪካዊ ጠላቶች ስውር ሴራ የተፈጠረ የትምህርቱ ዘርፉ በእጅግ የከፋ የሙስናና ብልሹ አሠራር ምክኒያት ታሪካዊ የትውልድ ውድቀት ውስጥ መግባቱ መሆኑን በመገንዘብና ቅድሚያ በመስጠት በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን አስመልክቶ በኢትጵያዊያን ገለልተኛ አጥኚ ባለሙያዎች በማስጠናት፣ በጥናቱ የተለዩትን አደጋዎች ለባለድርሻ አካላት የማሳወቅ ስራ በስፋት እየከወነ ሲሆን፣ ይህን ጥናት ጥቅምት 25/2015 ዓ.ም የተለያዩ ከፍተኛ የመንግስት አካላትና የሀይማኖት ተቋማትና የሲቪክ ማህበራት በተገኙበት ውይይት ማድረግ ችሏል። ይህን ውይይት በኢትዮጵያ ቴሌቪዢን የቀጥታ ስርጭት ለመላው ሀገሪቷ ህዝብ ማስተላለፍ የቻለ ሲሆን፣ በሌሎች ዘርፎችም ስራውን አጠናክሮ የሚሠራ ይሆናል።


ፀረ-ሙስና፣ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

አድራሻ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ቆይታ



**በኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ የወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከል የሀገርን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ሀገራዊ ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው። የወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ በስሩ በአራት ዋና ዋና ማለትም የወንጀል ምርመራ ኦፕሬሽን ዋና መምሪያ፣ የፎረንሲክ ምርመራ ም/ዋና መምሪያ፣ የታክቲክ ወንጀል ምርመራ ምክትል ዋና መምሪያ እና የሰው ኃይል አስተዳደር ድጋፍ አገልግሎት ምክትል ዋና መምሪያ እንዲሁም በድጋፍ ሰጭ ክፍሎች የተዋቀረ ነው።**

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የአራተኛ ዕትም እንግዳችን በኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ የታክቲክ ወንጀል ምርመራ ም/ዋና መምሪያ ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ ናቸው።**

**የዛሬው እንግዳችን በመምሪያው ስረጅም ጊዜ በማገልገል የሚገኙና ዘርፉን በኃላፊነት የሚመሩ ወንጀልን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ናቸው። የ€€ፀረ-ሙስና« ጋዜጣ ከረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች። መልካም ንባብ...**



**ረዳት ኮሚሽነር ብርሃኑ አበበ**

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- በኢትዮጵያ የሙስና ወንጀሎቾ በአሁኑ ወቅት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ፡-** በሀገራችን የሙስና ጉዳይ አሁን ባለው ሁኔታ ስር የሰደደ፣ አንዳንዴ ደግሞ የተፈቀደ በሚመስል መልኩ ወንጀለኞች ከጊዜ ወደ ጊዜ የወንጀል አፈፃፀም ዘዴያቸውን እየቀየሩና እየተበራከቱ አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ስለሆነም የሀገሪቷን ኢኮኖሚ ማዳከሙ እንደተጠበቀ ሁኖ ከዛም አልፎ ሙሰኞች በተጠናከሩ ቁጥር በኢኮኖሚ የዳበሩ ከሆኑ በጣሊያን ሀገር ላይ እንዳሉት የጣሊያን ማፍያዎች በመባል እንደሚጠሩት ሁሉ የኛወቹም እንደነሱ ላለመሆናቸው ዋስትና አይኖረንም።

በተመሳሳይ መልኩ ከአደዛዥ ዕፅ ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች የሀገሪቷን መንግስት የሚፈታተኑ ናቸው። በሙስና ወንጀል ላይ የተሚሳተፉ ግለሰቦች በህገወጥ መንገድ በሚያገኙት ገንዘብ ኢኮኖሚያቸውን በማፈርጠማቸው ምክንያት የመንግስት ባለስልጣንን በገንዘብ ኃይል የማይዙበት ምክንያት አይኖርም። በተጨማሪም በህገ ወጥ መንገድም ሰዎችን የማደራጀትና የማስታጠቅ ጉልበት በማፍራት መንግስትን የመገዳደር ሁኔታ ስለሚኖራቸው የሙስና ወንጀል አደገኝነት ሀገርን ሊያፈርስ በሚችል መልኩ ከሽብርተኛነት በበለጠ ድምፅ በማጥፋት ሀገሪቱን የሚያጠፋ የሽብረተኛ ወንጀል ነው ማለት ይቻላል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የሙስና ወንጀሎችን በመከላከል ሂደት ላይ የሚገጥማቹህ ተግዳሮት ምንድን ነው?**

**ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ፡-** በሀገራችን በጣም አብዛኞቹ ሙስኛ ሊባሉ የሚችሉት ከመንግስት ስራ ጋር ተያይዞ የህዝብን ሀብት ለግል ጥቅማቸው እንዳያውሉ በአዋጅ ቁጥር 881/2008 የመንግስት ባለስልጣንና ሰራተኞች ብቻ በሙስና እንዲፈረጁ መድረጉ ውጤት አያመጣም፤ በሀገሪቱ የወጡ የተለያዩ የሙስና ወነጀል ህጎች የመግስት ሰራተኞች ላይ ብቻ ያተኮሩ በመሆኑና መላውን ህብረተሰብ ያላካተቱ በመሆን ለፀረ ሙስና ትግሉ ከፍተኛ ክፍተትና ተግዳሮት ሆኖ በጠጨባጭ ይስተዋላል። ህጉ ራሱ መንግስት ሰራተኛን ለመቅጣት የተዘጋጀ ይመስላል እንጂ የሀገሪቷን ሙሰኞች ለመከላከል የወጣ አይመስልም። ትልቁ ነገር ሂዶ ሂዶ የሙስና ወንጀለኞች የሚበራከቱት ጥቅም ያለበት ቦታ ላይ ነው፤ ኮንስትራክሽን፣ ግባታና ከግብር ስወራ ጋር ተያይዞ የሀገራችን ገቢ የሚያሳጡ ከንግድ አለም ጋር ተያይዞ በሀሰተኛ ሰነዶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች በሀገራችን ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ወንጀሎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

ህገወጥ የገንዘብ ዝውውርን በተመለከተ አንዳንድ ሰዎች እስከ 22 የባንክ አካውንት እስከመክፈት የደረሱ ሲሆን ሲሆን፣ ግለሰቦች ምን ያክል የባንክ አካውንት መክፈትና ምን ያህል ገንዘብ ማንቀሳቀስ እንዳለባቸው ገደብ አልተቀመጠም፤ ሙስና ያተኮረው በተወሰነ የተደራጁና በኔትዎርክ በተሳሰሩ ግለሰቦችና ቡድኖች መሆኑ፣ ነገር ግን ከዚያ ውጭ ሌሎች የተፈቀደላቸው የግል ድርጅቶችና የግል ባለሀብቶች በህገወጥ የገንዘብ ዝውውር በመሳተፍ የራሳቸውን አካውንት እያቀሳቀሱ የሚያገኙትን ገቢ እየተጠቀሙ ለመንግስት የሚገባን ገቢ በማሳጣትና የግብር መሰወር እንዲሁም ሀብት ወደ ውጭ በማሸሽ ለሀገር የኑሮ ውድነትና የኢኮኖሚ ጫና ይፈጥራሉ።

አንዳንድ ግለሰቦች የዳበረ የንግድ እንቅስቃሴ ሳይኖራቸው ብዙ ገንዘብ ሲያንቀሳቅሱ ይስተዋላል። በቢሊዮንና በሚሊዮን በህገወጥ መልኩ የተለያዩ እቃዎችንና ህገ ወጥ የሙስና ወንጀሎችን ከተጎውጫሌ ያመጣሉ፤ የዚህ ገንዘብ ምንጩ ከየት መጣ ብለህ ስጠይቅ በህገወጥ መንገድ የሚዘዋወሩ ናቸው። ከዚህ ጋር ያለው የሙስና ወንጀል ሳይለት ነው።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- በሀገራችን የሙስና ወንጀሎች የሚስተዋሉት በየትኛው ዘርፍ ወይም አካባቢ ነው?**

**ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ፡-** በሀገራችን የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች ይሰራሉ ተብለው ትኩረት የተሰጠው የመንግስት ሰራተኛና ህዝባዊ ድርጅት ብቻ ላይ ነው፣ ግማሹን ህብረተሰብ ክፍል እንኳን አልያዘም፤ ህጉ የተነሳው ባለስልጣናቶች ወይም መንግስት ሰራተኞች በህገወጥ መንገድ ሀብት እንዳያፈሩ ለመከላከል፣ህብረተሰቡን እንዳያንገላቱ ለመከላከል ታስቦ የተደረገ ይመስላል እንጂ ሙሉ በሙሉ የኢኮኖሚውን ሴክተር ይዘው በህገወጥ መንገድ ሀብት የሚያፈሩ ባለሀብቶችን በሙሉ የሚያካትት ባለመሆኑ አደገኝነቱ የበረታ ነው።

የሙስና ወንጀሎች በብዛት በግዥ ስርዓት፣ ከመሬት፣ ግንባታና ኮንስትራክሽን እንዲሁም ከግብር ስወራ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ያመላክታል፤ ከዚያ አልፎ ደግሞ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አደገኛ እፆች ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በአሁኑ ጊዜ በመባባስ ላይ ናቸው። ይህን የሚሰሩትም በአየር መንገድ ላይ የሚሰሩ ሰራተኛ ናቸው። በዚህ የተሳተፉ 12 አካባቢ የሚደርሱ ግለሰቦች ታሰረው ምርመራ እየተደረገባቸው ይገኛል። ይህን ስራ የሚያከናውኑት ኔትወርክ ፈጥረው በግሩብ ሲሆን፣ በተለይ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ቡድን ወንጀሉ ላይ ተሳትፈዋል ተብሎ ምርመራ እየተጣራባቸው ይገኛል። ይህን ህገወጥ ድርጊት ወደ ሀገር ሲገባ መከላከል ይቻላል፤ ነገር ግን ህገወጦችን መቆጣጠር ሲገባቸው በህገወጥ መንገድ በማሳለፍ በዕለቱ የሚኖሩ ሰራተኞች በመመሳጠር ከህገወጦች ገንዘብ በመቀበል ይከፋፈላሉ፤ ስረቆቱ ከግለሰብ ወደ ቡድን ስራ እየሆነ ነው።

በተጨማሪም ከመሬት ወረራ ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ ካርታ የመስጠት፣ የገበሬ ልጅ ሳይሆኑ የገበሬ ልጅ ነኝ ብሎ ቦታ የመውሰድና የመሬት ተነሺ ሳይሆን ካሳ የመውሰድ የመሳሰሉ የሙስና ወንጀሎች የተስፋፉበት ሁኔታ ይስተዋላል፤ የተወሰኑት በአስተዳደር ጉዳዮች የሚፈቱ ቢሆንም የጊዜውን ጉዳይ ከለላ በማድረግ የሚፈጠሩ ወንጀሎች ናቸው፤ መንግስት በአንድ ነገር ሲጠመድ ሌቦች ወቅቱን በመጠቀም በሙስና ወንጀል ላይ በአቋራጭ የመበልፀግ አዝማሚያዎች ይታያሉ፤ ይህን በመሰለ ጉዳይ ላይ የፌደራል ፖሊስ ከአቃቢ ህጎች ጋር በመተባበር የሚመጡ ጥቆማዎችን ትኩረት በመስጠት እይሰራ ይገኛል።

ከአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮምሽን ጋር ተያይዞ የተፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች ብርቱ ትግል በማድረግ ምርመራው ተጣርቶ አንላይን ክስ እንዲመሰረት በማድረግ ተጠርጣሪዎቹ/ተከሳሾቹ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገቡ ተደርጓል። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ ከኮደሚኒየም እጣ አወጣጥ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ማስረጃዎች በመሰብሰብ ተጠርጣሪዎች የታሰሩ ሲሆን በተጨናነቀ ሁኔታ ውጤታማ ስራ ተሰርቷል።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከፍትህ ተቋማትና ከአጋር አካላት ጋር ያላችሁን ቅንጅታዊ አሰራር ቢገልፁልን?**

**ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ፡-** በአሁኑ ወቅት መንግስት ለሙስና ወንጀል ትኩረት በመስጠት ወቅታዊ ቡድን አቋቁሞ ከ40 ያላነሱ ኬዞች እየተሰሩ ይገኛሉ። በተለይ በኤርፖርት በኩል የውጭ እንቅስቃሴ ሳይኖራቸው በህገወጥ መንገድ ዶላር የሚያስገቡና ሀሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም እቃ ወደ ሀገር ቤት በማስገባት የሀገሪቷን ኢኮኖሚ የሚጎዱ ግለሰቦች መኖራቸው፣ እንዲሁም ዶላር ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባና ወደ ውጭ እንዲሸሽ በማድረግ የሚሳተፉ የተጠረጠሩ ግለሰቦች በመኖራቸው እንደቡድን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል።

ከቅንጅታዊ አሰራር ጋር ተያይዞ ከጠቅላይ አቃቢ ህግ ጋር ጥሩ ግንኙነት ሲኖረን በተለይ ቀደም ብሎ የፌደራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ወደ ተለያዩ ክፍሎች ሲበታተን የነበሩ ኬዞችን ትኩረት በመስጠት ቶሎ ውሳኔ እንዲያገኙ ለማድረግ እየሰራን ሲሆን፤ አሁን አንላይን ላይ ወቅታዊ ጉዳዮች በተለይም ተጠርጥረው የሚመጡ ተከሳሾችን ምርመራ አጣርተን ክሱን መሰረት በማድረግ ላይ በጋራ ይሰራል።

ሙስና ከገንዘብ ጋር ስለሚገናኝ በተለይ አንዳንድ ጊዜ የኦዲት ግኝትን ለማግኘት ግለሰቡ ሙስና በመፈፀሙ ምን ጉዳት አደረሰ የሚለውን ለማወቅ ኦዲትን እንጠቀማለን፤ ኦዲት አካባቢ የባለሙያ እጥረት በመኖሩ በራሳቸው እቅድ ላይ የማተኮር ነገር ሲኖር፣ ኦዲት በባህሪው በአጭር ጊዜ የሚያልቅ አይደለም፤ በፌደራል ዋና መስሪያ ቤት የሚሰራ ኦዲት እስከ ሶስት ወር ጊዜና ከዚያ በላይ ይዘገያል፣ ገቢዎችና ጉሙሩክ አካባቢ በ75 ቀን ውስጥ ያልቃል ተብሎ ይገመታል። በዚህ ምክኒያት የኦዲት ውጤት ሲጠበቅ ኬዞች ረዥም ጊዜ የሚዘገዩበት ሁኔታዎች ይኖራል፤ የኦዲት ስራው ቶሎ አለመጠናቀቅ እንደፈለግነው ለመስራት እንቅፋት ይሆንብናል።

ከፌደራል ስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮምሽን ጋር በተያያዘ ያለን የመረጃ ልውውጥ በጣም ጥሩ ነው፣ የጠየቅናቸው መረጃዎች ወዲያው ስለምናገኝ እንደ ችግር የሚነሳ ጉዳይ የለም። ስራው ሀገራዊ ጉዳይ ስለሆነ ፖሊስ ብቻውን ሰርቶ የሚያመየጣው ለውጥ አይኖረውም።

**የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ከመንግስት፣ ከፍትህ አካላትና ከህዝቡ እንዲሁም ከአጋር አካላት ምን ይጠበቃል?**

**ረዳት ኮምሽነር ብርሃኑ አበበ፡-** በአንድ ወቅት ሀገራዊ ንቅናቄ ይፈጠራል ተብሎ ለስራው ትኩርት በመስጠት ኮሚቴ ተዋቅሮ የተመለከትኩ ሲሆን ስራው ሲጀመር ህብረተሰቡ የሚያማርርበት ጉዳይ መፍትሄ ያገኛል ተብሎ ይታሰባል፤ ባለፈውም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲሾሙ ትኩረት እስጣለሁ ካሉት አንዱ የሙስና ዘመቻ ላይ ነው፤ ይሄ ሳንፈልግ የገባንበት ጦርነት ወደ ሌላ አቅጣጫ ወስዶን ነው እንጂ አንዱ አሁን ሀገሪቱ ከተረጋጋች በርግጠኝነት ዘመቻው ሙስናን ወደ መዋጋት እንደሚሆን አልጠራጠርም።

አሁን የተጀመሩ ነገሮች አሉና ይህ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ይህን ስናደርግ አጋዥ እናገኛለን፣ ህዝቡ መንግስት ቁርጠኝነቱን ካሳዩ ሙሰኞችን ከመጠቆም ወደ ኃላ አይልም፤ ፈራ ተባ የሚለው ብንጠቁም መልሶ እኔን ሊጎዳኝና ሊያጠቃኝ ይችላል የሚል አመለካከትና አስተሳሰብ ስላለው እንጂ መንግስት ከተጠናከረ፣ የፍትህ ተቋማትና መስሪያ ቤቶች ከተጠናከሩ እንዲሁም የሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት በጥምረት የሚሰሩ ከሆነ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

የተለያዩ የመንግስትና የግል ሚዲያዎችን እንዲሁም ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ለህብረተሰቡ የሙስና ወንጀል አደገኛነቱን፣ አስከፊነቱንና ህብረተሰቡን ሊጎዳ እንደሚችል ለማሳወቅ ፕሮግራም ተይዞለት አየር ላይ በማዋል ማስተማር ቢቻልና ህብረተሰቡን በማሳተፍ በቅንጅት ተባብረን መስራት ከቻልን ሙስናን መቀነስ ይቻላል።

# ሳይቃጠል በቅጠል

ሙስና የልማት እንቅፋት፣ የሰላምና መረጋጋት ጠንቅ፣ የህግ የበላይነት እንዲሸረሸር በማድረግ መሠረታዊ የሠብአዊ መብቶች እንዲጣሱና የዜጎች ፍትሀዊ የሀብት አጠቃቀም እንዲዛባ የሚያደርግ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግር ነው። ይህን የሠላም እና የእድገት ፀር የሆነውን የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግር በጠንካራ አደረጃጀት፣ በእውቀትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ መታገልና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ለነገ የማይባል የአገራችንን የህልውና ጉዳይ ሆኗል።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባርና የሞራል እሴት ግንባታን በማጠናከር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል፣ በአገር ደረጃ የማስተባበር ኃላፊነት ያለው ተቋም ነው።

ኮሚሽኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና ተቋማዊ ተልዕኮን ለመፈፀም ያስቻለው ዘንድ በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች፣ ማለትም፡- በስነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ዘርፍ፣ በሙሰና መከላከል ዘርፍና በተቋማዊ ለውጥ ማሻሻል ዘርፍ አሠራርና አደረጃጀት በማሻሻልና የሪፎርም ስራዎችን በማካሄድ ወደ ስራ ተገብቷል።

የዜጎችን ስነምግባር ከመገንባትና ሙስናን እንዲታገሉ ማድረግ በስነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ዘርፍ፣ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ማሰተባበሪያ መሪ የሰራ ክፍል፣ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና መሪ ስራ ክፍል እንዲሁም የሥነምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ክፍል ይገኙበታል።

በሙስና መከላከል ዘርፍ በኩል፡- የሙስና ስጋት ጥናት፣ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ የሙስና መረጃ እና የሃብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት መከላከል መሪ የስራ ክፍሎች ተዋቅረውበታል። ቀሪ ድጋፍ ሰጭ የስራ ክፍሎች ድግሞ በተቋማዊ ማሻሻያ ዘርፍ ውስጥ ተዋቅረው ለዋና የስራ ክፍሎች አሰፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ሆነው ተደራጅተዋል።

እነኝህ በስራ ባህሪያቸው ቅርበት የተደራጁት የስራ ክፍሎች በዘርፍ መደራጀታቸው እርስ በእርስ እንዲናበቡና አንዱ ለአንዱ ግብዓት በመሆን፣ በኮሚሽኑ የእውቀት ማኔጅመንት ስርዓት እንዲጎለብትና ሀገራዊ የስነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ስራውን በሚፈለገው መልኩ ለመምራትና ለማስተባባር የሚስያችል ነው።

በዚሁ አደረጃጀት መሰረት በ2015 የበጀት አመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ስነምግባር የመገባትና ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ይረዳ ዘንድ የስራ ክንውኖችን እንደሚከተለው ተመላክተዋል።

የሥነምግባር እና ሙስና መከላከል ሥልጠና ዘርፍ፡- በየጊዜው መልኩን እየቀየረ ህብረተሰቡን ለከፍተኛ ማህበራዊ ችግር እያጋለጠ ያለውን የተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል እንዲረዳ በአመራሩና ሰራተኞች የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ስራ በትኩረት መሥራትን ይጠይቃል። በዚሁ መሠረት በ2015 በጀት ዓመት በመጀመሪያ ሩብ ዓመት በትምህርት ዘርፍ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ዘርፍ እንዲሁም በፍርድ ቤቶች ዘርፍ በተካሄደው የሙስና ሥጋት ጥናት ሠነዶች ላይ ከፌደራል እስከ ወረዳ ባለው መንግስታዊ መዋቅር ሥር ባሉ በመንግስት ተቋማት ለተደራጁ ለ1,400 በላይ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች ግምገማዊ ሥልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም በሁሉም የክልል መስተዳድር ኮሚሽኖች የትውልድ ሥነምግባርና በሞራል እሴቶች ለ41,800 በላይ የህብረተሰብ አካላት ሥልጠና መሰጠቱን ከክፍሉ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በሩብ ዓመቱ በመንግስት ተቋማት የሚስተዋለውን የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች የመከላከል ሥራዎችንየመሥራትናየተቋማትየበላይአመራሮችን የማማከር አገልግሎት የሚሠጡ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በማደራጀት ወደ ሥራ ያልገቡ ወይም የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች የተጓዳለባቸው 635 ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን እንዲያደረጁና እንዲያሟሉ ድጋፍና ክትትል ተደርጓል።

በተጨማሪም የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች በየተቋሞቻቸው የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በተሟላ መልኩ አቅደው እንዲሰሩ ለማሰቻል በ385 ተቋማት የክትትልና ድጋፍ ስራ በመስራት፣ በሱፐርቭዥን ወቅት በታዩ ክፍቶች ላይ ማሻሻያዎችን እንዲያደረጉ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ተከናውኗል።

ይህም ሙስናና ብልሹ አሰራርን ተቋማት በራሳቸው አቅም እንዲከላለከሉ ለማስቻል በስነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ የተቋማትን አቅም የማብቃት አንዱ አካል ነው። በየተቋማቱ ትንንሽ የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችን ማዋቀሩ በራሳቸው አቅም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲከላከሉ ማስቻል ብቻም ሳይሆን የአመራሩንና የሰራተኛውን በስነምግባር መርሆ የመምራትና የማገልገል ስሜት ከፍ ወዳለ ደረጃ ያደርሳል።

ህብረተሰቡና የባለድርሻ አካላት በፀረ-ሙስና ትግል ላይ በባለቤትነትና በኃላፊነት ስሜት የትግሉ አካል እንዲሆኑ ለማስተሳሰር እንዲረዳ በፌደራልና በክልል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች 10 የትስስርና የትብብር መድረኮችን በማዘጋጀት በሥነምግባርና በፀረ ሙስና ዙሪያ ግንዛቤ በመያዝ የትግሉ አጋርና ተባባሪ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል።

በተጨማሪም በጥቅምት ወር ውስጥ በከፍተኛ የመንግስት ስራ አስፈፃሚዎች የስነምግባር ደንብ እና የጥቅም ግጭትን መከላለከልና ማስተዳደር ረቂቅ ደንብ ላይ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የመንግስት ስራ አስፈጻሚዎች በተገኙበት ቀርቦ የግብዓት ማሰባሰብ ስራ የተከናወነ ሲሆን፣ ረቂቅ ደንቡ የተዘጋጀው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 79(17)፣ በተሻሻለው የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 1236/2013 አንቀፅ 7(9) ና 23(1) መሰረት ነው።

በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይም ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያለቸው የተለያዩ ሀገራት የሚጠቀሙት የከፍተኛ የመንግስት ስራ አስፈፃሚዎች የስነምግባር ደንብ እና የጥቅም




ግጭት መከላከያና ማስተዳደሪያ ረቂቅ ደንብ ለተሞክሮ የቀረበ ሲሆን፣ በውይይቱም የተሻለ ግብዓት ማግኘት ተችሏል። ረቂቅ ደንቡ ፀድቆ ተግባራዊ ሲሆን የመንግስት ባለስልጣናት በጋራ እና በተናጠል ለሚሰጧቸው ውሳኔዎች በግልፅነት እና በተጠያቂነት መርህ እንዲሰሩ የተጣለባቸውን ህገ መንግስታዊ ግዴታ በተግባር የሚያረጋግጥ መሆኑ ተመላክቷል።

ደንቡ መፅደቁ ከፍተኛ የመንግስት የስራ አስፈፃሚዎች የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች ከሀገሪቱ እና ከህዝቦቿ ብሔራዊ ጥቅሞች ጋር የተያያዘ ስለሆኑ ይህንኑ ስራ በላቀ የሥነምግባር ደረጃ እንዲፈፅሙ ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

ኮሚሽኑ በጥቅምት ወር ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ካደረገባቸው ዘርፎች ውስጥ የትምህርት ዘርፍ አንዱ ሲሆን በዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችና መፍትሔዎች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በዚህም የትምህርት ዘርፉ የተጋረጠበትን የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግር ለመቅረፍ ሁሉም ማህበረስብ አስተዋፅኦ ማድረግ ሰለሚገባው ውይይቱ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተቀርፆ አየር ላይ እንዲውል በማድረግ ከፍተኛ ማህበረሳባዊ የግንዛቤ ማጎልበቻ ስራ መከናወኑ ተመላክቷል። በመሆኑም በቀጣይ ትርጉም ያለው ስራ ለመስራት ባለድርሻ አካላት በፀረ-ሙስና ትግሉ የድርሻቸውን እንዲወጡ አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በሙስና መከላከል ዘርፍም፡- የዘርፍ አደረጃጀትን መሰረት ባደረገ መልኩ በተቋማት ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮችና አደረጃጀቶችን በሙስና ሥጋት ጥናት በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለማመንጨትና በተቋማት የሙስና ቅነሳ ስትራቴጂ ተነድፎ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ መቻሉ ተመላክቷል።

በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በመንግስት ግዥ አፈፃፀም፣ ቀረጥና ታክስ አስተዳደር፣ በመንግስት ንብረት አጠቃቀም አስተዳደር፣ በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥና በመሳሰሉት ላይ ያተኮሩ የአሰራር ስርዓት ጥናት በማካሄድና የማሻሻያ ሀሳብ በማመንጨት በተቋማት ተግባራዊ እንዲሆን በመላክ የትግበራ ክትትልና ግምገማ ስራ የተከናወነ ሲሆን፣ ጥናቱ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ አሰራሮችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን የሚያመላከት በመሆኑ በአሰራር ስርዓት ምክንያት በተቋማት ውስጥ የሚፈፀመውን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በመንግስት ተቋማት ውስጥ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራርን ለማስፈን የተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በዲጂታል አሠራር (DARS) ሀብታቸውን የማስመዘገብና ማሳደስ ስራ ተሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪ የተመዘገበ የሀብት አስመዝገቢዎች መረጃ ትክክለኛነት በማረጋገጥ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሀብት ምዝገባ መረጃ ለማጣራት በቂ ምክንያት በተገኘባቸውና በተለዩ የ53 የሐብት አስመዝገቢዎች ላይ ከነቤተሰቦቻቸው በድምሩ 123 ያህል የሃብት ምዘገባ መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል። ይህም በመንግስት ተቋማት ውስጥ የግልጽነትና የተጠያቂነት አሠራርን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ነው።

ዜጎች በአገልግሎት ላይ የሚያገጥማቸውን የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን እንዲያቀርቡ አሠራር የተዘረጋ ሲሆን በሩብ ዓመት ውስጥ 365 የሙስና መረጃ ጥቆማዎች ከህብረተሰብ ለኮሚሽኖቹ መቅረቡ ተመላክቷል። በዚህ መሠረት የቀረቡትን የሙስና መረጃ ጥቆማዎች የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ በሐረሪ ክልል መስተዳድር በተለያየ ዘዴ ሊመዘበር የነበረው 26,926,223.8 (ሃያ ስድስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) ብር የመንግስትና የህዝብ ሀብት ጨምሮ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ አፈፃፀም ከ20 የፌደራል የመንግሥት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች እንዲሁም በ7 ክልሎች በተሰሩ አገራዊ የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራዎች 42,447,016.66 (አርባ ሁለት ሚሊዬን አራት መቶ አርባ ሰባት ሺ ከአስራ ስድስት ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም) ብር ከምዝበራ ማዳን መቻሉን በመስከረም ወር የፀረ-ሙስና ጋዜጣ ዕትም መረጃውን መግለፅ መቻላችን ይታወሳል።

የፌደራልና የክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የተጣለባቸውን መልካም ስነምግባር የመገንባትና ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የውስጥ አቅም የማጠናከርና አስቻይ ሁኔታዎችን የመፍጠር ስራም ተሰርቷል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር



## የተለያዩ የህግና የሙስና ወንጀል ፍትህ አስተዳደር ዘገባን በተመለከተ

በዚህ የጋዜጣ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና የተመረጡ የምርመራ የክስ የክርክር የፍርድና ከፍርድ በኋላ የሚከናወኑ በሙስና ወንጀል የተመዘበረውን የሀገር የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን አጠር አጠር ባለ ሁኔታ የሚቀርብ ሲሆን ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ኮንቬንሽኖችንና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡

- **ከዓለም ዓቀፍ ህጎችና ስምምነቶች አንፃር**

ሙስናና ብልሹ አሠራር በዓለማችን ህዝቦች የእስከዛሬ ታሪክ ለተፈጠሩ እጅግ አደገኛ ችግሮች እንደዋና መንስኤ ተደርጎ በመላው ዓለም ህዝቦች ሀገራትና መንግስታት መታመን ከጀመረ ውሎ አድሯል።

የአደጋውን አስከፊነት ማመንና ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን አደጋውን በጋራ መከላከል መዋጋትና መቀነስ ካልተቻለ ሊያስከትል የሚችለው የሠው ልጆች ጥፋትና የኋላቀርነት፣ የድህነት፣ የጦርነት፣ የሠላም እጦት፣ የሠብዐዊ መብት ጥሰት፣ የህግ የበላይነት መጣስ፣ የዴሞክራሲ እጦት፣ የዜጎች ስደትና የኑሮ መፈናቀል፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመንና የአየር ንብረት መበከል፣ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልና በዜጎች መሀከል ተመጣጣኝ እድገት አለመኖር፣ የልማት ኋላ ቀርነትና ሌሎች ያልተጠቀሱ የከፉ አደጋዎች እየተባባሱ እንደሚሄዱ በማመን የጋራ መፍትሄ ወደ መፈለግ ሊገባ ተችሏል።

አደጋውን በጋራ መከላከልና መዋጋት አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ከሚያረጋግጡ ምክንያቶች ውስጥ ወንጀሉ በአንድ ሀገርና አህጉር ክልል የሚወሰን ሳይሆን ድንበር ተሻጋሪ አደገኛ ወንጀል መሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ ይህን ዓለማቀፋዊ አደጋ በጋራ ለመከላከልና ለመዋጋት በዓለማችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ሀገራችን ኢትዮጵያም የተሳተፈችበት ጉባኤ በሪዞሉሽን ቁጥር-58/4 አክቶበር 30/2003 እኤአ መሠረት የተባበሩት መንግስታት የፀረ ሙስና ኮንቬንሽንን UNCAC / United Nation Convention Against Corruption / በተለያዩ አባል ሀገራት ስምምነት ተደርሶበት ከተፈረመና ከፀደቀ በኋላ ከዲሴምበር 14/2005 እ.ኤ.አ ወደ ተጨባጭ ትግበራ ገብቷል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም ኮንቬንሽኑን ታህሳስ 10/2003 ከፈረመች በኋላ ህዳር 26/2007 እ.አ.አ በማፅቅ ወደ ስራ የገባች ሲሆን በፌደራል ህገ መንግስቷም በአንቀፅ-9 እና በአንቀፅ-13 በመደንገግ የሀገሪቱ ህጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ህግ መንግስት አካል አድርጋ በተጨባጭ በኮንቬንሽኑ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን እየተገበረች ሲሆን በህገ መንግስቷ ከማካተት ባለፈ ወደ ተግባር ለመፈፀም እንዲቻል በሀገሪቱ የበላይ የህግ መወሰኛ ምክር ቤት በሆነው ፓርላማ አዋጅ ቁጥር-544/2007 ዓ.ም እንዲሁም የአፍሪካ ህብረት የፀረ ሙስና መከላከያና መዋጊያ ኮንቬንሽ ፈራሚ አባል ሀገር በመሆንዋ በተመሳሳይ ሁኔታ የህብረቱን ስምምነት የህገ መንግስቷ አካል ከማድረግ ባለፈ በአዋጅ ቁጥር-545/2007 ዓ.ም በማውጣት ኮንቬንሽኖችን በተጨባጭ እየተገበረች ትገኛለች።

ለኮንቬንሽኖቹ አፈፃፀምና ትግበራ የተለያዩና ብዛት ያላቸው የህግ ማዕቀፎችን ያወጣች ሲሆን የወጡትንም ህጎች የሚያስፈፅሙና የሚያስተገብሩ ብዛት ያላቸው ተቋማትን ያደራጀች ሲሆን አዋጅ ቁጥር-433/1997 ዓ.ም የፌደራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ አንዱና ዋናው ሲሆን 12ቱም የክልል መንግስታት የየራሳቸውን የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖችን እንዲያቋቁሙ መደረጉ ሀገሪቱ በኮንቬንሽኖቹ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን በተጨባጭ በመተግበር ዙሪያ ከወሰደቻቸው ጠንካራ እርምጃዎች ውስጥ አንዱና ዋናው ነው።

የፌ/ሥ/ፀ/ሙ/ኮሚሽንም ሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን በመከላከልና በመዋጋት ዙሪያ የማስተባበር ሀላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል። በኮንቬንሽኑ ከተደነገጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱና ዋናው ሀገራት ኮንቬንሽኑን እንዴት እየተገበሩ እንዳሉ በየአምስት ዓመቱ በሌሎች ሀገራት የሚገመገሙ ሲሆን ሀገራችንም የመጀመሪያውን አምስት አመት ግምገማ በ International Co-opration And Criminalization ላይ በማልታና በቶጎ ተገምግማ ግብረ መልስ ተሰጥቷት እየተገበረች ሲሆን ሁለተኛውን ዙር ግምገማ በዚህ ዓመት 2015 ዓ.ም Corrption Prevention And Asset Ricovery ላይ በግሪክና በኮንጎ ብራዛቢል የምትገመገም ሲሆን የአምስት አመት አፈፃፀም ሪፖርቷንም አጠናቅቃ አስትሪያ ቬና ለሚገኘው ዋና ፅ/ቤት ልካለች። ቀሪውን በህዳር ወር ጋዜጣ እትም ለንባብ ይበቃል...

## ከፖሊስ የሙስና ወንጀል ምርመራ ዘገባ

በዚህ ክፍል በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል ምርመራ ቢሮ የቀረቡ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችና የተደረጉ የምርመራ ስራዎች የሚገለፁ ሲሆን ከነዚህ ምርመራ ስራዎች ውስጥ ከፍተኛ የሙስና ወንጀል ሆነው ከጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ጋር በመቀናጀት በከፍተኛ ሳይንሳዊ የምርመራ ብቃት ለውጤት የበቁ የምርመራ መዝገቦች ለህብረተሰቡ መረጃና ግንዛቤ እንዲሆኑ ለዓብነት የሚገለፁ ይሆናል።

የፌደራል ፖሊስ ከሚመረምራቸው ከፍተኛና ከባድ ሀገራዊ ወንጀሎች ውስጥ የሙስና ወንጀል አንዱና ዋናው ሲሆን በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት በክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የተደረጉ ከፍተኛ የሙስና ወንጀል ምርመራዎችን ሳይጭምር 77 ጥቆማዎች የደረሱት ሲሆን ከነዚህ ጥቆማዎች ውሥጥ 55 ጥቆማዎች በመንግስታዊ ተቋማት የተፈፀሙ በመሆኑ እነዚህን ጥቆማዎች በመንግስታዊ ተቋማት የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን ለሚከታተለው የምርመራ ክፍል ተልኮ እየተመረመረ ሲሆን ቀሪዎቹ 25 የምርመራ መዝገቦች ደግሞ በመንግስት ልማት ድርጅቶችና የግል ህዝባዊ ድርጅቶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን ለሚከታተለው የምርመራ ክፍል ተልኮ በመመርመር ላይ ይገኛሉ።

የፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ ከፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ጋር በሩብ ዓመቱ ከመረመራቸውና ለውጤት ካበቃቸው ከፍተኛ ሀገራዊ ከባድ የሙስና ወንጀል ምርመራ መዝገቦች ውስጥ በአስተማሪነት በጋዜጣው ቢታተሙ የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ ከተባሉት ውስጥ የሚከተሉትን ለዓብነት ለማሳየት ተሞክሯል፡-

- በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል የአርሶ አደር ኮሚቴ አመራር ሆነው የሚሰሩ አካት ከመሬት አስተዳደር አመራሮችና ሠራተኞች ጋር በመመሳጠር ከህግ ውጭ አርሶ አደር ያልሆኑ ግለሰቦችን አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጆች እንደሆኑ በማስመሰል ሠነድ አዘጋጅተው በጠቅላላ 3500 ካ.ሜ የመንግስት ቦታ ለግለሰቦች መብት እንዲፈጠር አድርገዋል በሚል የቀረበ የምርራ መዝገብ መጣራቱን ተገልፃል፤
- የሞጆ ጉምሩክ ኮሚሽን ሠራተኞችቭ የሆኑ ከባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር በህግ የተፈቀደለትን የፕላስቲክ ዕቃዎች ጥሬ ዕቃ ማስገባት እንዳስመጣ በማስመሰል የመዋቢ ዕቃዎችን እንዲያስገባ አድርገዋል በሚል የቀረብ የሙስና ወንጀል ምርመራ እየተተጣራ መሆኑን ተገልፃል፤
- የኢሚግሬሽንና የዜግነት እና ወሳኝ ኩነቶች ኤጀንሲ ሠራተኞች ከኤጀንሲው አሠራርና መመሪያ ውጭ ለተለያዩ ግለሰቦች ፓስፖርት መስጠታቸው ተጣርቶ ለዓቀቤ ሕግ ቀርቦ ክስ የተመሠረተ መሆኑ ተጠቅሷል፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ስል/ቴክ/ል/ቢሮ እና አ/አበባ/ከተ/አስ/ቤቶ/ኮርፖሬሽን የቤት መረጃ ዳታ ቤዝ በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃ ተመድበው ሲሰሩ ከሌሎች ግብረአበሮች ጋር በመመሳጠር ሀምሌ 01 ቀን 2014 ዓ.ም ዕጣ ከወጣው የጋራ መኖሪያ ቤት ጋር ተያይዞ የማጭበርበር ስራዎችን በመስራት ዕጣው የሚመለከታቸው ደንበኞች ቀርተው የማይገባቸው ግለሰቦች እንዲወጣላቸው በማድረግ ዓለም ዓቀፍ ስታንደርድ ያልጠበቀ ኤሌክትሮኒካል ሲስተም ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ ከኢንሳ ምንም አይነት ማረጋገጫ ያልተሰጠውን ቴክኖሎጅ በመጠቀም የፈፀሙት ከባድ የሙስና ወንጀል ከፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ጋር የተቀናጀ ምርመራ በማድረግ ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራቸው ተጣርቶ ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑ።
- በአባይ ባንክ የተለያዩ ቅርንጫፎችና የተለያዩ ከተማዎች በመዘዋወር ሀሰተኛ ስሞችን በመጠቀም ከ 10,000,000,000/ አስር ሚሊዮን ብር / በላይ ወጪ አድርገው ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ተጠርጣሪዎች ምርመራ መዝገብ ተችሏል፤
- በፋይናንስ መረጃ አገልግሎት ውሥጥ ቡድን መሪ ሆኖ የሚሠራ ተጠርጣሪ ስልጣኑን በመጠቀም ከወቅታዊ ስራዎች ጋር በተያያዘ የባለ ሀብቶችን የባንክ ሂሳብ አሳግዳለሁ ፤ በወንጀል የተጠረጠሩ መሆኑን በመግለፅ እንዳይታገድባችሁ ገንዘብ እንዲከፍሉ ማድረግና የሀበሻ ሲሚኒቶ ፋብሪካ ጋር በተያያዘ ሀብትን ከሀገር በማሸሽ በፋይናንስ ደህንነት ተሰርቶበት የተጠረጠረ ግለሰብን ምርመራ እንዳይሰራ በማድረጉን ከሚያገኘው ገቢ ጋር የማይመጣጠን በራሱ ስም፤ በባለቤቱ ስም፤እና በቤተሰቦቹ ስም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ያፈራ ተጠርጣሪ ምርመራ መዝገብ ተችሏል፤
- በፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሀላፊ ሆኖ የሚሰራው ተጠርጣሪ የተለያዩ የምርመራ መዝገቦችን ተጠቅሞ ከተለያዩ ግብረአበሮቹ ጋር በመመሳጠር ብር 7,000,000,000 / ሠባት ሚሊዮን / ብር በተቀበሉ ሃላፊና ተባባሪዎቻቸው ላይ በስልጣን አለአግባብ መገልገልና ያልተገባ ጥቅም ማግኘት ከባድ የሙስና ወንጀል ምርመራ የተጣራባቸው

መሆኑ የሚሉትና ሌሎች ከዚህ በታች በጠቅላይ ዓቃቤ ህግ የተገለፁ የክስ መዝገቦች በፖሊስና በዓቃቤ ህግ በጋራ ተመርምረው ውጤታማ ከሆኑት ውስጥ ለአብነት መጠቀሱን ከፌደራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ቢሮ ያገኘነው መረጃ ተመላክቷል፡፡

## ከዓቃቤ ህግ የሙስና ወንጀል ክስ ዘገባ

በዚህ ክፍል በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ የሙስና ወንጀሎች ክትትል ክፍል የቀረቡ የሙስና ወንጀል ክስ መዝገብ ስራዎችና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር የህዝብና የመንግስት ሀብትና ገንዘብ በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎች የሚገለፁ ሲሆን ከነዚህ የክስ ስራዎች ውስጥ ከፍተኛ የሙስና ወንጀል ሆነው ከፌደራል ፖሊስ ጋር በመቀናጀት በከፍተኛ ሳይንሳዊ የምርመራ ብቃት ለውጤት የበቁ የምርመራና የክስ መዝገቦች ለህብረተሰቡ መረጃና ግንዛቤ እንዲሆኑ ለዓብነት የሚገለፁ ይሆናል፡፡

በመሆኑም በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከተፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችና ምርመራቸው ተጣርቶ ለፍርድ ቤት ክስ ከቀረበባቸው መዝገቦች ውስጥ የሚከተሉትን ለምሳሌ ማሳየት የተሞከረ ሲሆን ለነዚህ ከባባድ ወንጀሎች ለህግ ፊት መቅረብ ከመነሻ ጥቆማ ከመስጠት ጀምሮ የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠትና ምስክር ሆኖ ወንጀሉን በማስረዳትና አጠቃላይ የምርመራ ስራው ተሳክቶ ለክስ እንዲቀርብ በማድረግ ዙሪያ የህብረተሰቡ ተሳትፎ እጅግ ከፍተኛ ሲሆን ይህን ፅሁፍ የሚያነቡ የሕብረተሰብ ክፍሎችም በቀጣይነት ተመሳሳይ ተግባር በመፈፀም ለሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራር መዋጋትና ሙሰኞችን ለፍርድ በማቅረብ ዙሪያ ከፍትህ አካላት ጋር በርብርብ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ከኮንደሚኒየም እጣ አወጣጥ ጋር በተያያዘ በተፈፀመው ማጭበርበር በተሳተፉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ ሙያ ስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ሀላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ሠራተኞች ምርመራ መዝገብ ተጣርቶ በ11 ተከሳሾች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቧል፡፡
- በፍርድ ቤት የተሰጠን እግድ እናነሳለን በሚል በፍትህ ሚኒስቴር ሠራተኞች ስም 15 ሚሊዮን ብር ጠይቀው 7.8 ሚሊዮን ብር ጉቦ ከመቀበል ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል በተጠረጠሩ የፍትህ ሚኒስቴር የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሀላፊ ዓቃቤ ህግና ተባባሪዎቻቸው ላይ ምርመራ ተጣርቶ ክስ ቀርቧል፡፡
- ከባንክ ገንዘብ ማጭበርበር ጋር ተያይዞ በምርመራ ላይ የሚገኝ የሙስና ወንጀል መዝገብ ላይ ገንዘብ ካላመጣህ ዋስትና በሚያስከለክል አንቀፅ እንድትከሰስ መዝገቡን ለፖሊስ አስተላልፋለው በማለት ገንዘብ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ በተያዘ በሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ውስጥ የሚሠራ ዓቃቤ ህግ በቁጥጥር ስር ውሉ ምርመራ ተጣርቶበት ክስ ተመስርቷል፡፡
- ያለውን ስልጣን ተገን በማድረግ የባለሀብቶችን እና ድርጅቶቻቸውን የባንክ ሂሳብ አስቀድሞ በማጥናትና መረጃዎችን በመውሰድ ባለሀብቶቹ በሚሊዮን ብሮች ገንዘብ እንዲከፍሉ በመጠየቅ የማይከፍሉ ከሆነ ደግሞ የፋይናንስ እንቅስቃስያቸውን በተመለከተ ምርመራ አድርጎ ጉዳዩን ለፖሊስ የሚያስተላልፍ መሆኑን በማስፈራራትና ጫና በመፍጠር ከባለሀብቶች ከ3.5 ሚሊዮን ብር በላይ በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ውስጥ የፋይናንስ መረጃ ክትትልና ቅበላ ቡድን መሪ እና ተባባሪዎቹ ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቷል፡፡
- ሀሰተኛ ውክልናዎችን እና መታወቂያዎችን በመጠቀም የግለሰቦችን መኖሪያ ቤት በተጭበረበረ መንገድ ከ45 ሚሊዮን ብር በላይ በመሸጥ ቅድሚያ 15 ሚሊዮን ብር ገንዘብ በተቀበለ ግለሰብ ላይ ምርመራ ተጣርቶ በከባድ የሙስና ወንጀልና ህገወጥ ገንዘብን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ከባድ የሙስና ወነጀል ክስ ተመስርቶበታል፡፡
- በህይወት የሌሉና ውጭ ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በባንክ ያላቸውን ለረዥም ጊዜ ሳይንቀሳቀስ የቆየ ሂሳብ ደንበኞች እንዳሉና እንደቀረቡ አስመስለው በማንቀሳቀስና ገንዘቡም ለሌሎች ሠዎች በማስተላለፍ በድምሩ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ በመውሰድ ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ ሰባት የአዋሽ ባንክ ሠራተኞች ላይ አራት ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡
- ከመሬት ሙስና ጋር በተያያዘ በሩብ ዓመቱ በተሰራው ስራ በ 5 መዛግብት በ46 ተከሳሾች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ከሚሰሩ ዋና ዋና ስራዎች ውስጥ በሙስና ወንጀል የተመዘበሩ የመንግስትና የህዝብ ሀብትና ገንዘብ የማስመለስ ስራ ሲሆን ይህም ስራ በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ የሆኑ ግለሰቦችን የፍርድ መዝገብ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ክስ በመመስረትና በማስፈረድ የሚሰራ ሲሆን በሩብ ዓመቱ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ጀነራል የሚከተሉትን የአፈፃፀም ክሶችን ከሶ በማስፈረድ ከዚህ በታች የተጠቀሱ ገንዘብና ሀብቶችን ማስመለስ ችሏል፡፡

በሩብ ዓመቱ ከተሰሩ ስራዎች መካከል 11 መዛግብት ላይ የአፈፃፀም ክስ በቀረበባቸው ላይ መዛግብት ላይ ክትትል በማድረግ ብር 49,868,465.44(አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ስድሳ አምስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) ለመንግስት ገቢ ተደርጓል፡፡

የተመዘበረ ንብረት ማስመለስን በተመለከተ የዋጋ ግምታቸው ብር 2.5 ሚሊዮን የሚገመት 2 ተሽከርካሪዎች እና የአንዱ ኮንቴነር ዋጋ 7000 ዶላር የሚያወጣ ብዛት 17 40 ፊት ኮንቴነሮች ተወርሰዋል፡፡

<u>ለማሳያ ያክል፡-</u>

1. እነ አልፋሮክ በተከሰሱበት የወንጀል ክስ በሀሰተኛ ሰንድ በመጠቀም ከቀረጥ ነፃ መብት እንዲኖር በማድረግ በጉምሩክ ላይ ለደረሰው የ36,700,000 ብር ጉዳት በወንጀል የተያዘው ንብረት ተሸጦ ገንዘቡ ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
2. በዚሁ መዝገብ 33 ኮንቴነሮች የሚፈለጉ ቢሆንም የተያዙት 17 ኮንቴነሮች ለኢትዮጵያ ባህርና ሎጂስቲክስ አገልግሎት እንዲመለሱ ተደርጓ፡፡
3. እነ ቢዮ ኃላ/የተ/የግል ድርጅት በተጠረጠሩበት የሙስና ድርጊት ከዚህ ቀደም በተደረገ ድርድር መሰረት 13 ሚሊዮን ብር ገቢ ተደርጓል፡፡

   ምንጭ- በፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀሎች ክትትል ሚኒስትር ዴኤታ ስራ ክፍል፡፡

በሙስና ወንጀል ልዩ ባህሪነት የተነሳ ስለሚገደቡ የሰው ልጆች መሠረታዊ መብቶች ምን ያህል ያውቃሉ፤

የዋስትና መብት፤ / Right to Bail VS Prohibition of Bail /

የዋስትና መብት በተባበሩት መንግስታት ሠብዐዊ መብት ሠነድ ላይ ከተጠቀሱ መሠረታዊ የሠው ልጆች መብቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም በፌደራል ህገ መንግስቷ ውስጥ በክፍል አንድ ስር ከተደነገጉ መሠረታዊ የማይጣሱና የማይገሰሱ መብቶች ውስጥ የዋስትና መብት በአንቀፅ-19 ንዑስ አንቀፅ -6 ላይ ደንግጋለች፡፡

እነዚህ መሠረታዊ የሠው ልጆችን መብት አጠባበቅ አስመልክቶ ከሙስና ወንጀል ውጭ በሆኑ ልሎች መደበኛ ወንጀል ፍትህ አስተዳደርና አፈፃፀም ሂደት የሚከበሩ ሲሆን በልዩ ሁኔታ ብቻ በከባድ የግድያ ሙከራ ወንጀል ወቅት ብቻ የተጎጂው ህይወት ሊያልፍ ይችላል የሚል ጥርጣሬና እምነት ሲኖር ብቻ የዋስትና መብትን ህጉ ይገድባል፡፡ ከዚህ ውጭ ባሉ ማናቸውም ወንጀሎች የዋስትና መብት የማይጣስና የማይከለከል የማይገደብ መሠረታዊ የሠው ልጆች መብት ሲሆን የሀገራችን ፍትህ ስርዐትም ይህን መሠረታዊ የሠው ልጆችን መብት በጥብቅ ይተገብራል፡፡

ነገር ግን ከሙስና ወንጀል እጅግ ልዩ ባህሪና አፈፃፀሙም እጅግ ውስብስብ ሆኖ ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ባላቸውና ሀብት ገንዘብ እውቀት ባላቸው ግለሰቦች ኔትዎርክ የሚፈፀም በመሆኑ በመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዐት ህግ መምራትና ምርመራውን ማስኬድ እጅግ አስጋሪ ከመሆኑም በላይ የሙስና ወንጀል በሀገር ህልውና ላይ የሚያስከትለው አደጋ እጅግ የከፋ በመሆኑ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በምርመራ ላይ ያሉና በክስ ሂደት ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በዋስትና ቢለቀቁ የሚፈጠረው ችግርና ወንጀሉን የመሰወርና የተለያዩ መረጃዎችን መሠወርና ከሀገር የመጥፋትና ሌሎችንም የማድረግ አቅሙም የተሳሰረ ኔትዎርክም ስላላቸው ይህን መሠረታዊ የዋስትና መብት መገደብ በማስፈለጉ የተለያዩ ሀገራት ይህን የመብት እገዳ አድርገው በወንጀል ፍትህ ስርዐታቸው በህግ በማውጣት እየተገበሩ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም ከመደበኛው የወንጀል ስነ ስርዐት በተለየ ሁኔታ የሙስና ወንጀልን የሚመራበት ልዩ የሙስና ወንጀል ምርመራ የሥነ ሥርዐት ህግ ያወጣች ሲሆን በዚህ ልዩ የስነ ሥርዐት ህግ ውስጥ ከተደነገጉ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ውስጥ ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪና ተከሳሾችን የዋስትና መብት ሙሉ በሙሉ በመከልከል የሙስና ወንጀልን በጥብቅ በመዋጋትና ፈፃሚዎችን በጥብቅ ተከታትሎና መርምሮ ለፍርድ በማቅረብ ዙሪያ ከወሰደቻቸው ጥብቅ እርምጃዎች ውስጥ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡



...በህገ ወጥ መንገድ የህዝብንና የመንግስትን እምነት ክደው በፈፀሙት ሙስና ያካበቱት ሀብትና ንብረቶቹ ተወርሰው ለመንግስት ገቢ የሚሆኑ ይሆናሉ...

የንብረት ማፍራትና በሚስጥር የመጠበቅ መሠረታዊ የሠው ልጆች መብትና የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ግዴታ /Right of Property VS Duties of Asset Registration/

የዜጎች የንብረት ማፍራትና በሚስጥር መጠበቅ መብት በሙስና ወንጀል ጉዳይ ተገድቦ ለምን ሀብታቸውን እንዲያሳውቁ ይደረጋል?

የንብረት ማፍራትና ያፈሩት ንብረት በሚስጥር የመጠበቅ መብት በተባበሩት መንግስታት ሠብዐዊ መብት ሠነድ ላይ ከተጠቀሱ መሠረታዊ የሠው ልጆች መብቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም በፌደራል ህገ መንግስቷ ውስጥ በክፍል አንድ ስር ከተደነገጉ መሠረታዊ የማይጣሱና የማይገሰሱ መብቶች ውስጥ በአንቀፅ-41 የደነገገች ሲሆን በፍትህብሄር ህጓም በማካተት እየተገበረች ትገኛለች፡፡

የንብረት ማፍራትና ያፈሩት ንብረት በሚስጥር መጠበቅ መብት በዋናነት መሠረታዊ የሠው ልጆች መበት ሆኖ ከማይገረሰሱና ከማይጣሱ መብቶች ውስጥ እንዲካተት የተደረገው ሠዎች ያላቸውን እውቀት ጉልበት ገንዘብና ሀብት ተጠቅመው በነፃነት ለራሳቸውና ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ሀብትና ንብረት እንዲያፈሩና ራሳቸውም ተጠቅመው ሌሎችን እንዲጠቅሙ ታስቦ ሲሆን ይህ ደግሞ የሚሆነው በነፃነትና ያለማንም ጣለቃገብነትና ከለላና ገደብ በፈለጉት ኢኮኖሚ መስክ ተሠማርተው ንብረት እንዲያፈሩ ብቻ ሳይሆን ያፈሩትንም ሀብትና ንብረት በነፃነት እንዲያዙና ከራሳቸው ውጭ ማንም ሀብትና ንብረታቸው ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባና በሚስጥር እንዲጠበቅ የህግ ጥበቃ እንዲደረግላቸውም ጭምር ነው፡፡

ነገር ግን የሙስና ወንጀል በዋናነት የሚፈፀመው በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት የመንግስት ተሠዋሚዎች ፤ ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች በመሆኑና ከእነሱ ጋር ትስስር ባላቸው የተለያዩ አካላት ጭምር በመሆኑና በሙስና የሚዘርፉትንም ሀብትና ንብረት በተለያዩ መንገዶች እንዳይታወቅባቸው በዘመዶቻቸው በቤተሰቦቻቸውና በሌሎች ሠዎች ስም የሚሰውሩ በመሆኑና ይህ ደግሞ ሀገሪቱን እጅግ ለከፋ አደጋ ከመዳረጉም በተጨማሪ የፀረ ሙስና ትግሉን ክፉኛ ከማደናቀፉም ባለፈ በሙስና የተዘረፈ ሀብትን በማስመለስ ሂደት ከፍተኛ ችግር ከመፍጠሩም በተጨማሪ የዚህ ተግባር ፈፃሚ የሆኑ የመንግስት ባለስልጣናትና የመንግስት ሠራተኞች ከሚያገኙት ህጋዊ ገቢ በላይ ሀብትና ንብረት ከማካበት ባለፈ በሚያውቃቸው ህብረተሰብ ውስጥ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ከፍተኛ ሀብትና ንብረት አፍርተው እንደፈለጉት እንዲኖሩ ከማስቻሉም ባለፈ ህብረተሰቡ በመንግስት ላይ እምነት ከማጣት ባለፈ ተስፋ ወደ መቁረጥና በፀረ ሙስና ትግሉ የራሱን ድርሻ እነዳያበረክት ስለሚያደረግ የዜጎች ሀብትና ንብረት የማፍራትና ያፈሩትን ሀብት በሚስጥር የመጠበቅ መሠረታዊ መብት ለአጠቃላይ ሀገር ህልውና ሲባልና የፀረ ሙስና ትግሉን በከፍተኛ ህግ ማስከበር ቁርጠኛ እርምጃ መቆጣጠር በማስፈለጉ ይህ መብት ተገድቦ የመንግስት ባለስልጣናት ተሿሚዎች ተመራጮችና የመንግስት ሠራተኞች በራሳቸውና በቤተሰቦቻቸው በዘመዶቻቸው ስም ያፈሩትን ሀብትና ንብረት እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ያስመዘገቡትንም ሀብትና ንብረት ምንጩ ከታወቀና ህጋዊ በሆነ መንገድ ስለማፍራታቸው እንዲያረጋግጡ እንዲገደዱ ይደረጋል፡፡

ማረጋገጥ ካልቻሉ ደግሞ በፈፀሙት ተግባር ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማፍራት ወይም ከገቢ በላይ ሀብት ማፍራት ሙስና ወንጀል ተከሰው ለፈፀሙት ተግባር ህጋዊ ቅጣት ይፈፀምባቸዋል፡፡ በህገ ወጥ መንገድ የህዝብንና የመንግስትን እምነት ክደው በፈፀሙት ሙስና ያካበቱት ሀብትና ንብረቶቹ ተወርሰው ለመንግስት ገቢ የሚሆኑ ይሆናሉ ሀገራችን ኢትዮጵያም በፌደራል የስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በኩል ይህን ተግባር እየፈፀመች ሲሆን በሌሎች የተለያዩና በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ባደጉ ሀገራት ግን ሀብትና ንብረትን የማሳወቅና የማስመዝገብ ግዴታ የመንግስት ባለስልጣናትና የመንግስት ሠራተኞች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጎች የሚያፈሩትን ሀብትና ንብረት የማስመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን በዚህ የተነሳ ማናቸውም ዜጎች ያፈሯቸውና የሚያፈሯቸው ሀብትና ንብረቶች በህጋዊ መንገድ ስለሚመዘገቡ በሙስና ወንጀል የሚፈሩ ሀበትና ንብረቶችን የመሰወር ወንጀል ዝግ ሲሆን የሙስና ወንጀል አደጋም በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ መንግስታቱም የሀገራቸውን አጠቃላይ ሀብት መረጃ በግለሰቦችና በመንግስት በተለያዩ አካላት የተያዙትን በማወቅ ለተለያዩ የፖሊሲ ውሳኔዎች የሚጠቀሙ ሲሆን እንደ ሽብርተኝነትና ሌሎች አደገኛ ድንበር ዘለል ወንጀሎችን በገንዘብና ሀብት የመርዳትን ስውር ወንጀልን በቀላሉ መቆጣጠርና ማስቆም ያስችላቸዋል፡፡ ቀሪውን ማብራሪያ በቀጣይ እትም ይጠብቁን ...

## ኪነ-ጥበብ


# ከሰው ማሣ አትጨድ!

ከሰው ማሣ አትጨድ!

ከሰው ማሳ አትጨድ --የንጥቂያ ከፍታ መሬት ታውላለች፡
እያንዳንዷ ውጤት --እያንዳንዷ ፍሬ ዋጋ አስከፍላለች፤
ጥረህ ግረህ ብላ --እንደ መፅሐፉ ቃል፡
ዛሬም ባይሆን ነገ --የሰው ወዙ ያንቃል፤
አፈሩን ጎልጉሎ --ቆፍሮ አረስርሶ፡
ዘርቶ ተንከባክቦ --ከእንቅልፉ ቀንሶ፤
ለዝናብ አንጋጦ --ፀሐይን ተማልዶ፡
መዳፉን አሻክሮ --ልምዱን አዋሕዶ፤
በውኑም በእንቅልፉም --ሲያስብ ከርሞበታል፡
ፍሬው እስኪያፈራ --ሥቃይ ቆጥሮበታል፤
ከሰው ማሳ አትጨድ!
በጨለማ ተገን --እንዳይቀጨው አውሬ፡
እንዳያደባየው --ረግጦ ተራምዶበት ግድ አይሰጠው ጥሬ
አጥሮ ጠብቆት ነው --ውጤት ሆኖ አብቦ ይህ ያየኸው ዛሬ፤
እያንዳንዷ ውጤት --እያንዳንዷ ፍሬ ዋጋ አስከፍላለች፡
ከሰው ማሳ አትጨድ --የንጥቂያ ከፍታ መሬት ታውላለች፤
ጥረህ ግረህ ብላ --እንደ መፅሃፉ ቃል፡
ዛሬም ባይሆን ነገ --የሰው ወዙ ያንቃል፤
በግንባር፡ በላብህ በጉልበትህ ጥረት --በራስህ ተመንደግ በድካምህ ውጤት
ከሰው ማሣ አትጨድ --ዝም ብሎ አላፈራም እንዲያው እንደዘበት፤
ዘለህ አትፈሰው፡
ንቀህ ወይ ዘንግተህ የደከመበትን የፈጠረውን ሰው፤
በየቱም ሙያ መስክ --በምንም ሥራ ላይ ደክመህ መመንደግ ነው --ከልብ የሚያረካው .. ስትውል
ከበላይ ጤና ተገብሮ ተስፋ ተሰንቆ፡
በቁር በሐሩሩ --ተጥሎ ተወድቆ፤
የጋሬጣ ፍቀት --ያደማ እሾህ ታልፎ፡
የለማ ፍሬ ነው --ከዕድሜ ላይ ተቀርፎ፤
ከሰው ማሣ አትጨድ!

ከገጣሚና አርቲስት አለምፀሐይ ወዳጆ

# መልካም ዜጋ




**ጥሩ የሚባሉ ህጎች በርካታ የሥነምግባር ደረጃዎችን ያካተቱ ቢሆንም፣ ጥሩ ውሳኔ ህግ እና መመሪያን መሰረት ያደረገ ብቻ ሳይሆን ሥነምግባራዊ ተገቢነት ያለው እና ሥነምግባራዊ መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ነው**

# አመራርነት በተምሳሌትነት ይገለጥ

ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲፈፀም በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋናው ምክንያት የስነምግባር ዝቅጠት ነው። መልካም ስነምግባር በሰፈነበት ተቋም ሙስናና ብልሹ አሰራር ሲቀንስ፣ ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶች ባሉበት ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራር ተባብሶ ይቀጥላል፤ በመሆኑም ስነምግባርና ሙስና ጥብቅ ቁርኝት አላቸው።

በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች እና የሥራ መሪዎች መጠኑ ይብዛም፣ ይነስም የህዝብ ሃብትና ንብረት ላይ የመወሰን ስልጣን አላቸው። ወሳኙ አካል ውሰኔዎችን ሲያሳርፍ ምንን መነሻ ያደርጋል የሚለው ትልቅ ጉዳይ ነው። አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ የተቋም ፍላጎት፣ ሀገራዊ ጥቅም ወይስ የግል ፍላጎት፤ የቤተሰብ ጥቅም፣ የቡድን ጥቅም ወይስ ሌላ?

መሪዎች በአስተዳደር ስርዓታቸው ከራሳቸው ይልቅ ሀገርን በማስቀደም መስራት እንዳለባቸው ይጠበቃል። ለዚህም ነው መሪነት በበጎ ተፅዕኖ ተከታዮችን ለጋራ ዓላማና ራዕይ ማሰለፍ ነው የሚባለው። በጎ ተፅዕኖ ማሳደር የሚቻለው ደግሞ እንዲሁ ዝም ብሎ ሳይሆን ራስን ቀድሞ ማሸነፍ (first drop your ego) በመቻል ነው።

የስነ ልቦና ምሁራን እንደሚያስቀምጡት ራስን የመውደድ/ራስን የማሸነፍ ደረጃ በሶስት መልኩ ይገለፁታል።

የመጀመሪያው ራስን ከመውደድ ያለፈ ለራስ ብቻ ማሰብ (Id Ego) ይባላል፣ ይህ የራስ ወዳድነት ደረጃ በህፃንነት እድሜ ደረጃ ከሚገኙ ጋር ይመሳሰላል። በዚህ የእድሜ ደረጃ ያሉ ህፃናት አጠገባቸው ያለውን፣ በርቀት ያዩትን በአጠቃላይ ለስሜት ህዋሳቸው ቅርብ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ለራሳቸው የማድረግ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው። ያዩትን ነገር አምጡ፣ እኔ ካልወሰድኩት ብለው ያለቅሳሉ፣ ሁሉንም ነገር መቆጣጠር ይሻሉ አልቅሰወም ይጠቀማሉ። አልፎ ተርፎ ሰው ይዞት ያዩትን ሁሉ ይመኛሉ፣ ያለቅሳሉ፣ ይወስዳሉም። ይህም የስነልቦና ልሂቃን እንደሚሉት ጤናማና (normal) ማንኛወም ሰው የሚያልፍበት የተፈጥሮ ህግ መሆኑን ነው። ነገር ግን በእድሜ ደረጃቸው ከፍ ያሉ፣ በትምህርት ደረጃቸው አዋቂ የሚባሉ እንዲሁም በኃላፊነት ደረጃ ያሉ ሰዎች ሲፈፅሙት ከመደበኛ ስርዓት ውጭ በመሆኑ ከጤናማ (normal) ወደ ጤናማ ወዳልሆነ (abnormal) ስነ-ልቦና ይሸጋገራል። ሂደቱና ድርጊቱም ዝቅጠት ይባላል። በእድሜአቸው ትልቅ ሆነው እንደትንሾቹ ማሰብ፣ ብዙ ተምረው እንደማያውቁት ሆነዋልና፣ በኃላፊነት ደረጃ ተቀምጠው አርአያ መሆን ተስኗቸዋልና።

ኃላፊነት አደራ ነው፤ በአግባቡ እንዲጠብቁ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲያገለግሉ፣ በአደራ እና በቃለ መሀላ ጭምር የተሰጣቸውን ኃላፊነት፣ አደራውን ትተው ስልጣናቸውን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም በአደራ የተቀበሉትን የህዝብ ሃብትና ንብረት የሚዘርፉ፣ ስልጣናቸውን ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት የሚጠቀሙ፣ በህፃንነት የእድሜ ደረጃ ከሚገኙ ልጆች ተርታ ይመደባሉ። አሁናዊ የሀገራችን ሁኔታ ከዚህ በተለየ መልኩ የሚታይ አይደለም።

ሁለተኛው መልክ ራስን መውደድ ነው፤ ራስን መውደድ ጤናማ ነው፣ ለራስ ማሰብ ለሌሎች አለማሳብ ማለት አይደለም፤ እንዲያውም ለሌሎች ማሰብ የሚቻለው በቅድሚያ ራሰን መቀበል ሲቻል ነው።

ሶስተኛው መልክ ደግሞ ሱፐር ኢጎ ነው፤ ሱፐር ኢጎ ከራስ አልፎ ለሌሎች ማሰብ ነው፤ ይህ መልክ እኔ የማስፈልገው ለእኔ ብቻ ሳይሆን ከእኔ ውጭም ላሉ ጭምር ነው የሚል ደረጃ ላይ የደረሰ ምልዑ አስተሳሰብ ነው። ባለኝ እውቀት፣ ባለኝ ጊዜ እና ባለኝ ኃላፊነት ለሌሎችም መድረስ አለብኝ፣ የሚሉና ያላቸውንም የሚተገብሩ ግለሰቦች የያዙት መልክ ነው። ከዚህ ደረጃ የደረሱ ግለሰቦች ለሌሎች በአርአያነት የሚታዩ፣ ፊት ለፊት እንደሚያበራ አምፖል የሚታዩ አብሪ ኮኮቦች ናቸው።

በአርአያነት ግለሰቦች ከሚከተሏቸውና በተምሳሌትነት ከሚታዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ መሪወች ይገኙበታል። መሪነት አርአያ በመሆን ሰዎችን ለጋራ ዓላማ እና ግብ በማነቃቃት እና መልካም ተጽዕኖ በማሳረፍ በፍቃደኝነት እንዲያሳኩ ማድረግ የመቻል ጥበብ ነዉ። መሪ የግለሰብን እና የቡድኖችን ባህርያት ወደ ታለመዉ ዓላማ አቅጣጫ ማምጣት የሚችለው ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥን በተግባር ማዋል ሲቻል ነው።

ውሳኔ በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ መፍትሄ የሚፈልጉ ጉዳዮችን ወይም ችግሮችን በጥንቃቄ መለየት፣አማራጭ መፍትሄዎችን መፈለግ፣ የተሻለ አማራጭ የመምረጥ እና የመተግበር ሂደት ነው። ውሳኔ ወደ ተግባር የሚለወጥ በመሆኑ በትኩረት የማሰብ፣ የመምረጥ እና ከህግና ከተገቢነት አኳያ የመወሰን ጉዳይን ይመለከታል።

መሪዎች በየቀኑ የተለያዩ ውሳኔዎችን ይወስናሉ፣ ውሳኔያቸው የሚመሯቸውን ግለሰቦች፣ የተቋሙን ሀብት እና ንብረት፣ አሰራር እና ተገልጋዮችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ውሳኔያቸው ትክክል እና ስህተት፣ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ፤ ፍትሃዊ እና ፍትሃዊ ያልሆነ ባህሪን እና ተግባርን ከመለየት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሁሉም ውሳኔዎቻቸው ሥነምግባራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው።

ሥነምግባር በህይወታችን የሚገጥሙንን አስቸጋሪ ምርጫዎችን ወይም ውሳኔዎችን በሚገባ አሰላስለን እንድንመርጥ እና ውሳኔ እንድንወስን የሚረዳን መርሆ ነው።

መሪዎች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ወይም በሚመሩት መስክ/ተቋም በእለት ተእለት ተግባራቸው ማድረግ የሚገባቸውን መወሰን ሲጠበቅባቸው፣ በአንድ በኩል የሚገጥማቸው ችግር ትክክል እና ስህተቱን፣ ጥሩ እና መጥፎውን፣ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆነውን ፍትሃዊ እና ፍትሃዊ ያልሆነውን የመምረጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ትክክል/ተገቢ ከሆኑ ምርጫዎች ይበልጥ የተሻለውን የመምረጥ የሥነምግባር ፈተና ነው። ይህን በተመለከተ አርስጣጣሊስ የሥነምግባር ማእከላዊ ነጥብ በእለት ተእለት ህይወታችን ውሳኔ ለሚጠይቁ ጉዳዮች «ምን ማድረግ ይገባኛል» ለሚለው ተግባራዊ ጥያቄ መልስ መስጠት መቻል ነው ይላል።

ስለዚህ ሥነምግባራዊ ውሳኔ ማለት በእለት ተእለት ተግባሮቼ ወይም በአንድ በተለየ ሁኔታ ውስጥ ማድረግ በሚገባኝ ነገር ወይም መወሰን በሚጠበቅብኝ ወቅት ምን ማድረግ ይገባኛል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ከጥሩ እና ከመጥፎ፣ ተገቢ ከሆነ እና ካልሆነ የመምረጥ፣ የመወሰን እና የመተግበር ሂደት ነው።

ሥነምግባራዊ ውሳኔ ህግ እና መመሪያን ተግባራዊ ከማድረግ የዘለለ ነው። መሪዎች በተለመደው መንገድ በህግ እና መመሪያ የማይሸፈኑ ውስብስብ እና ሥነምግባራዊ አጣብቅኝ ጉዳዮች ሲያጋጥሟቸው ለሥነምግባራዊ ውሳኔ የሚያበቋቻን ጉዳዮች ማጤን ይኖርባቸዋል። ስለሆነም እሴቶችን መሰረት በማድረግ አማራጭ መፍትሄዎችን የማቅረብ፣ የመምረጥ እና ውሳኔ ላይ የመድረስ ሂደትን በመለማመድ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ ተግባራትን ማከናወን አለባቸው። መሪዎች ሲሆን ሥነምግባራዊ ውሳኔን ለመወሰን ግላዊ፣ ቡድናዊ እና ተቋማዊ እሴቶችን፣ የሥነምግባር ደረጃዎችን እንዲሁም ተቋማዊ ራዕይ፣ ተዕእኮ፣ ዓላማና ግብ ወደ አንድ የውሳኔ አማራጭ የማምጣት ምክንያታዊ ሂደትንም መተግበር ይኖርባቸዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት መሪዎች ለውሳኒያቸው ህግ እና መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በቂ መስፈርት ተደርጎ ይወሰድ ነበር፤ ጥሩ የሚባሉ ህጎች በርካታ የሥነምግባር ደረጃዎችን ያካተቱ ቢሆንም፣ ጥሩ ውሳኔ ህግ እና መመሪያን መሰረት ያደረገ ብቻ ሳይሆን ሥነምግባራዊ ተገቢነት ያለው እና ሥነምግባራዊ መርሆዎችን መሰረት ያደረገ ነው። የአመራር ውጤታማነት በመሰረቱ የሚወሰነው የውሳኔ አሰጣጡ ተገቢነት እና ለውሳኔው መሰረት የሚያደርጋቸው የስነምግባር መስፈርቶች ወይም ሞራላዊ መርሆዎች ናቸው።

ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ የውሳኔ አማራጮችን ከሦስት አቅጣጫዎች ይመለከታል። ከሥነምግባራዊ ግዴታዎች፣ ለሌሎች ከማሰብ ሥነምግባር እና ከሥነምግባራዊ ምክንታዊነት አንጻር ነው። ሥነምግባራዊ ግዴታዎች ለህግ ካለ ግዴታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ህጉ ያካተታቸው ሥነምግባራዊ እና ሞራላዊ እሴቶችን ሲመለከት፣ ለሌሎች ማሰብ ስነምግባር ለሌሎች ያለንን በጎ አመለካከት እና በሌሎች ላይ የሚሰጥ ውሳኔን ራስን በሰዎች ቦታ አድርጎ ማየትን ይመለከታል። ሥነምግባራዊ ምክንያታዊነት ደግሞ ምክንታዊ አስተሳሰብ መጠቀም እና ውሳኔን በበቂ ምክንያት ላይ መመስረትን ይመለከታል።

ሥነምግባራዊ ውሳኔ ሁለት መሠረታዊ መርሆዎችን መቀበልን ይጠይቃል። አንደኛው ሁሉም መሪዎች የመወሰን እና ውሳኔውን ተግባራዊ የማድረግ አቅም እንዳላቸው እና ውሳኔው ሊሚያስከትለው ውጤት ኃላፊነት የመውሰድ የሞራል ግዴታ እንዳለባቸው መቀበልን ይጠይቃል። መሪዎች የሚወስኑት ውሳኔ ወደ ተግባር የሚለወጥ በመሆኑ በተቋም ተልዕኮ፣ ዓላማ፣ ግብ፣ አሴቶችን በመጠበቅ ላይ፣ በተገልጋዮች እና በባለድርሻ አካላት ላይ፣ እንዲሁም በሠራተኞች ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል። ለዚህ ውጤት ወሳኔ ሰጪው አካል ኃላፊነት ሊኖረው ይገባል።

ሌላው መሪዎች የሚፈተኑበት በኃለፊነት ለስራ ማሰኬጃ በሚወሉ የህዝብ ሃብትና ንብረት አጠቃቀም ዙሪያ ነው። በኃላፊነቱ ምክንያት በአንድ ግለሰብ እጅ የገቡ ንብረቶች የኢትዮጵያዊን ሁሉ ናቸው። መኪናው፣ ቢሮው፣ ስልኩ ወንበር ጠረጴዛው ወዘተ በሙሉ። ደብዳቤ የሚፅፍባቸው እስክርቢቶና ወረቀት ጭምር። ሙስናና ብልሹ አሰራር በቀነሳበቸው እስካንዲኒቪያን ሀገራት የመንግስት አመራሩና ሠረተኛው የህዝብ ሃብትና ንብረት አጠቃቀምን አሰመለክቶ በተለምዶ የሚነገረላቸው ምስክርነት አለ “ሁለት አሰክረቢቶ አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ ጆሯቸው ይይዛሉ”። አንደኛው ለመንግስትን ስራ ሌላኛው ለግል ጉዳይ መፈፀሚያ ። ለግል ጉዳየቸው የህዝብ ሃብትና ንብረትን መጠቀም እንደነውር ይቆጥሩታል። እኛ ኢትዮጵያዊያንስ? በመርህ ደረጃ የስራ ኃላፊነትን መሰረት አድርገው ባለስልጣናት የሚያስተደድሯቸው የህዝብ ሃብትና ንብረት በሙሉ ለስራው ሲባል ስራና ተግባራት የሚፈፀምባቸው፡ ለመፈጸም እንዲገለገሉባቸው የተሰጡ እንጅ ግለሰቡ የግል ህይወቱን የሚያመቻችባቸው አይደሉም። ይሁን እንጅ በሀገራችን እየታየ ያለው ሃቅ የዚህ ተቃራኒ ነው። የተቋም ንብረት ለሚፈለገው ስራና አገልግሎት ሳይሆን ለራሳቸው የግል ጉዳይ የሚያውሉ ሃላፊዎች ብዙዎች ሆነዋል። ስልጣን በባህሪው ማገልገያ እንጅ መገልገያ አይደለም። ይልቁንም ለማገልገል የሚሰጥ አደራና ኃላፊነት እንጅ ራስን ለመጥቀም ወይም ግለሰቦችን ለመጥቀም ለሌሎች የሚበረከት የልደት ስጦታ አይደለም።

ሥነምግባራዊ ውሳኔ ምክንያታዊነትን የሚመለከት በመሆኑ ሥነምግባራዊ መሪዎች ለውሳኔ ምርጫቸው መሠረት የሚደርጓቸው መርሆዎች ሊኖራቸው ይገባል። በመሆኑም በግል ጥቅምና ፍላጎት ተሸንፈን የግል ህይዎትን በማድለብ በቅንጦት ባህር ለመዋኘት የሚገፋፉንን ኢድ አጎ አሸንፈን በእጦት እየተንገላታ እምነት ለጣለብን ህዝባችንን እናስብ በአርአያነትና በተምሳሌትነትም እንምራው። በቀጣይ ወር ዕትም ለውሳኔ መሰረት በመሆን የሚያግዙ ሥነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃወችን እንመለከታለን።